ምዕራፍ 4

ኑሮን ቀለል አድርጋችሁ ኑሩት!

(አትጠላለፉ)

ምዕራፍ አራት

ኑሮን ቀለል አድርጋችሁ ኑሩት (አትጠላለፉ)

"ስለዚህ ወንድሞቻን ብታላስብ፣ በአምነትና በተከተልኸው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመግብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ይሆናል። ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመጥና የአርኒቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። ለግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ ለግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተሰፋ ስላለው፣ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" (1 ጢሞቴዎስ 4፣6)።

የወንጌል አማኞች ሁላችንም ከጌታ የተቀበልነው እና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እያደረግን አሁን በሥጋ የምንኖረው ሕይወታችን የተፈታ እና ነጻነት ያለበት እንዲሆን እንፈልጋለን። በነገሮች ሳንጠላለፍ፤ ጌታን እንደሚገባ በመውደድ እያመለክነው እና ፈቃዱን እያደረግን በደስታ መኖር የሁላችንም መሻት እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለኝም። የሁላችንም ፍላጎት ይሄ ቢሆንም፤ ኑሯችን ግን እንዲያ አይደለም። ከባድ እና የተወሳሰበ፤ እንዲያውም ውጥንቅጡ የወጣ ነው። ውሉን ስንፈታው ይተበተባል፣ ስናላቅቀው እንደገና ይጣበቃል፣ በአንዱ ወገን ስናቀለው በሌላው በኩል ከበዶ እናገኘዋለን። የአሁኑ ትውልድ ሰዎችን "አታካቢድ" ሲሉ ትሰሟቸዋላችሁ። እንዲያውም "ያካብዳሉ" ለሚባሉ ሰዎች "አካብዴ" የሚል ቅጽል ተሰጥፎላቸዋል።

ይህ አንጋር ቀደም ባለው ትውልድ ውስጥ አልነበረም። የቃሉ ትርጉም ሕይወት በፈትም ከብዷል እና አሁን ደግሞ አንተ የባስ አታከብደው ለማለት ነው። ኑሮ ቀለል እንዲል ነው የሚፈለገው። ለነገሩ የሥልጣኔ አንዱ ግብ ኑሮን ማቅለል አይደል! እነዚህ አዳዲስ የመጡት ቴክኖሎጂዎች በሙሉ ካያችኋቸው እንዱ ሥራቸው ነገርን ማቅለል ነው። ይሁንና ኑሮን ለማቅለል ብለን የምንወስዳቸው ርምጃዎች መልሰው የበለጠ ትኩረታችንን የሚሰቡ እና ሕይወትን የሚያወሳስቡብን ሆነዋል። ስልክ ገዝተው እንደገና የሚመልሱ ሰዎች ስንቶች ናቸው? ቀለል ያለ ስልክ ይገዙና በኋላ ላይ ያ የገዙት ራሱ ቀላሉን ነገር ሲያወሳስብባቸው "ነመን በጤና" ብለው ይመልሱታል።

ሰምሳሌ ኮምፒዩተርን እንውሰድ። ኮምፒዩተር የምንገዛው እና የምንለገልበት ነገሮችን እንዲያቀልልን ነው። ነገር ግን ከገዛነው በኋላ "እንዲህ ዓይነቱን ሶፍት ዌር አስገባ፣ ይሄን ፕሮግራም ጫንልኝ፣ ያንን እንዲህ አድርገው" ብሎ ሲያዘን፤ ዐላማችን ነገርን ማቅለል ስለሆነ የኮምፒዩተር ባለሙያ እንጠራና "ቀለል አድርጎ መጠቀም አይቻልም ወይ?" ብለን እንጠይቀዋለን። ሁላችንም ብንሆን ቀለል እንዲልልን ነው የምንፈልገው።

ትዳር ያልመሠረቱ ሰዎች "የብቸኝነት ኑሮ ስለከበደኝ ሚስት ወይም ባል ማግባት አፈልጋለሁ" ይላሉ። ትዳር ለመመሥረት ይሄ አንዱ ትልቁ እና በቂ ምክንያት ነው። ካገቡ በኋላ ደግሞ "መጋቢ፥ ኑሮን አልቻልኩትም። እንዲቀል ብዬ ባገባም መልሶ ይበልጥ ከበደኝ" ይላሉ። ሕይወታችን እንዲቀል ብንፈልግም ሰናቀሰው ይከብዳል፤ ስናላላው ደግሞ ይጠቅቃል። ግን ይህ ለምን የሚሆን ይመስላችኋል? ጌታ በመጀመሪያ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩፥28 ላይ ወደ እርሱ ሲጠራን *"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ . . ."* ብሎ ነው የጠራን። ይሄ ምን ማለት ነው? እናንተ ኑሮ የከበደባችሁ፤ አልቀል ብሏችሁም እየተውተረተራችሁ ካሁን አሁን ወደቀ እየተባለላችሁ የምትኖሩ ሰዎች ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ፤ አቀልላችኋለሁ ማለቱ ነው።

ሁላችንም ወደ ጌታ የመጣነው በዚህ ጥሪ ነው። የተሰበከልን ሰብከት "በላይህ ላይ ቀንበር እጭንበሃለሁ" የሚል ሳይሆን፤ "ቀንበርህን አውርጄ አሳርፍሃለሁ፤ ከዚያም ቀሊሉን የእኔን ቀንበር ትሸከማለህ" የሚል ነው። እኔ ጌታን የተቀበልኩት በዚህ ሰምምነት ነው። የእናንተም እንዲሁ እንደሆነ አስባለሁ። ጌታን ከተቀበልን በኋላ ግን "ይሄ ቀሊል ነው፣ አረፍት አለው፤ ጠላትህ ዶግ አመድ ይሆናል" የተባለው ሕይወት ግን ሳናውቀው ውስብስብ ብሎ ይጠመጠምብናል፤ ይከበድብናል፤ ነገሩ መካበድ ይጀምራል፤ ሳናውቀው ሕይወት አፍንጫችንን እየሰነገ እና እየተጠላለፈብን እንሄዳለን። ዶግ አመድ ይሆናል የተባለው ጠላትም ቁጥሩ በእጥፍ ጨምሮ ቁጭ ይላል። ከዚህ የተነሳ በምሬት "በፊት እኖረው የነበረው ሕይወት ይሻለኝ ነበር እንዴ?" ብለን እስከንል ድረስ ነገሩ እየተካበደ ይመጣል። "ይሻላል ያሉት ኩል ዓይን አጠፋ!" እንዲሉ አበው።

የክርስትና ሕይወትን መኖር ከጀመርን በኋላ ሳናውቀው በተለያየ ነገር እየተሳሰርን ነው የምንመጣው። የዚህ ዓለም ኑሮ፣ ሐሳብና ምኞት፣ እንዲሁም ከቤተሰብ እና ከባልንጀሮቻችን ጋር ያለን ግንኙነት ማቆሚያ ስለሌለው ውጥንቅጡን ለማስተካከል

እና በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት እንጥራለን። ሰው በዚህ ምድር በሕይወት እስካለ ድረስ ኑሮ ሁልጊዜ እየከበደ፣ እየተሳሰረ እና እየጠበቀ ነው የሚሄደው። አሁን እንዴ ወንድማችን ኑሮ እንዲቀልለት ጸሞ፣ ጸልዮ በዚህም በዚያም ብሎ አሜሪካን እገር ቢሄድ ይቀልለታልን? አንዲያውም "ትሻልን ፈትቼ፣ ትብስን አገባሁ እንዲሉ" የሄዱ ሰዎች እንደሚናገሩት እዚያማ ውጥንቅጡ የባሰ ከባድ ነው። ሰው ኑሮውን ቀለል ለማድረግ ብሎ የሚያደርገው ነገር በሙሉ እንዴ ከሌላው እየተቃየጠ ይበልጥ እባዜው እየጨመረበት እና እየተወሳሰበበት ነው የሚሄደው። ቀን ከሌሊት የምንጸልየው፣ ምከር የምንጠይቀውና የምንደከመው እኮ የተጸጠረውን የኑሮ ቋጠሮ ለመፍታት እና ነጻነት የሰፈነበት ሕይወት ለመኖር ነው። ይሁንና አውነቱን ካየነው ግን ኑሮ የባሰ እየጠበቀ፣ እየገረረ፣ እየመረረ ነው የሚሄደው።

አሜሪካን እገር የገቡ ሰዎች "የአኔን ችግር ጌታ ያውቀዋል፤ አንድ ብቻ ነው። አንድ መኪና ባገኝ ኑሮ ይቀልልኝ ነበር" ሲሉ ይደመጣሉ። ይሁን አንጂ መኪና ሲያገኙ ቀጥሎ ኢንሹራንሱ ይመጣል፣ ሌላም ሌላም ነገር እየተከታተለ በእናት በእናቱ ከች ይላል። ቀጥሰው ለአነዚህ ነገሮች ሁሉ ማሰብ እና መጨነቅ ይጀምራሉ። ከዚያም መኪናዋ ብር ከማስወጣት እጅ አስከ ማስጫን ታደርሳለች። ኑሮ እየከበደ ሲመጣ ጊዜያችንን ለቤተሰብ ለመስጠት፣ ሥራ ለመሥራት፣ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ፣ ከጓደኞቻችን ጋር ለመሆን እያዳገተን ሕይወት ውስብስብ እያለብን ወዲህና ወዲያ የምንባክን ባተሌዎች እንሆናለን። እና ምን ይሻላል? እያችሁ አንድ ሰው አንድን ነገር ሲያስር ቀስ ብሎ አንደ ዋዛ ይሆናል የሚያሰረው። በኋላ ለመፍታት ሲፈልግ ግን አስቦ ነው መፍታት ያለበት።

ቋጠሮው ውሉ ሲጠፋ፣ ሸብ ተደርጎ የታሰረው ጠብቆ፣ ቆንጥጦ፣ ለመሳብ ሲያስቸግር፣ ሽምቅቆው ተውሸልሽሎ፣ ተውተፍትፎ ውሉ የጠፋ ልታቂት ሲሆን፤ ሕይወትም እንዳንዴ እንዲሁ ናት። በሕይወታችን ውስጥ እንደ ቀልድ ገብተን የተሳሰርንበት እና ኑሯችንን ያካበድንበት ስንት ነገር ይኖር ይሆንን? አሁን "ከዚያ ውስጥ ልውጣ" ስንል ግን ጊዜን፣ ማሰብን የሚጠይቅ ነገር ሆኑብን። በጌታ ፊት ሆኜ ከተማርኩት ከዚህ ትምህርት በመነሳት የተለማመድኩትን አላስፈላጊ ነገር "እምቢ!" በማለት እንደገና መፍታት፣ መደምሰስ ያለብኝ ነገር ምንድነው? የሚለው የግል ጥረትን ያጠይቃል። ኑሯችንን ያካበዱብን እነዚህ ነገሮች ከእኛ ጋር ከመጣበቃቸው እና እኛን አስረው ከመያዛቸው የተነሳ ከእነዚህ ነገሮች ለመላቀቅ እና ለመለያየት በግል ተግዳሮቱን

መጋፈጥ እና *መታገል* ያስፈልጋል።

ስለዚህም ከዚህ በኋላ በቃ! ብሰን እንደ ቀላል ነገር በአፋችን የምንናገረው ነገር ብቻም ሳይሆን *መሥራት*ን፣ ጉልቡት ማፍሰስን፣ ቁጭትን፣ ውሳኔን፣ ቁርጠኝነትን፣ መጨከንን የሚጠይቅ ነው።

"ቀላል ያለችው ቤተ ክርስቲያን (Simple Church)" የሚለውን መጽሐፍ የጻፉት ጸሐፊ 1077 ለዎችን "ሕይወት ምን ይመስላል? በሕይወታችሁ አንዲሆን የምትፈልጉትስ ነገር ምንድነው?" ብለው ሊጠየቋቸው ጥያቄዎች ሁሉም የሰጡት መልስ "ሕይወት ቀላል አይደለም፤ በጣም ከባድ ነው" የሚል ነው። ሰዎቹ "እንዲቀልላችሁ የምትፈልጉትስ ነገር ምንድነው?" ሲባሉ "የምንፈልገው የመጀመሪያው ነገር የከበደብን ኑሮ እንዲቀልልን ነው። ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት፣ የገዝብ ጉዳይ፣ ቤተሰብን ማስተዳደር፣ ንብረት መያዝ፣ መንፈሳዊ ነገር ተወሳስቦብናልና፤ ኑሮን ቀለል ሊድርግ መኖር ነው የምንፈልገው" ብለው ነው የመለሱት።

የእነዚህ ሰዎች ችግር የእኛስ ችግር አይደለም ወይ? እንግዲያው ከተወሳሰቡብን ነገሮች ወጥተን የተፈታ ሕይወት ለመኖር ኦሯችንን የምናቀለው እንዴት ነው?

ቀሊልነት (Simplicity) ምንድነው? ቀሊልነት የሚለው ይህ ቃል "እከሌ ቀላል ሰው ነው፤ እከሊትም ቀላል ሴት ናት"፤ ከሚለው ለሰው አክብሮት መንፈግን (አልቦ ክብር/disrespectful) በሚያሳይ አሉታዊ ትርጉሙ ሳይሆን በአዎንታዊ ጎኑ አልቦ ንብርብር ወይም ምንም ዓይነት ውስብስብነት እና ውጥንቅጣዊነት ሳይታይበት ጠሊቅ ምርምር ወይም ፍተሻ ሳያሻው እንዲሁ በገሃዳዊ አይታ አውነታው ሰርዶ በሚታይ መልኩ ታሰተውሉት ዘንድ እፈልጋለሁ።

ለዚህም ነው Simplicity (ሲምፕሲሲቲ) ለሚለው የአንግሊዝኛ ቃል ይህን ቀለልነት የሚለውን ቃል የተጠቀምኩት። ቀሊል ሲባል ያልተጠማዘዘ፣ ቅን የሆነ፣ ያልተወላገደ ወይም ቀጥ ያለ እንዲሉ።

በ1828 ዓ.ም የታተመውና "ዌብስተር" የተሰኘው የአንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት መፍቻ Simplicity (ሲምፕሲሲቲ) ወይም ቀሊልነት የሚለውን ቃል እንዲህ በማለት ፍቺውን ይሰጣል። "ነጠላ፣ ያልተነባበረ፣ ወጥ-ሕይወት፣ ቀጥ ያለ፣ ቅን፣ አንድ ነገር ላይ

ብቻ ያተኮረ፣ ወዲህ እና ወዲያ የማይባጅ፣ በአለምሮ ውስጥ ያልተደበላለቀ ነገር መያዝ ማለት ነው" ይለዋል።

ቅንነት ከአለምሯችን ጋር በልባችን ውስጥ ካለው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ቅንነት ብለን ካልን ወደ ውስጥ ብቻ ነው የምናለገባው። ወርቅን "የጠራ ወርቅ ነው" የሚያስብለው ንጹህ እና ያልተደባለቀ መሆኑ ነው። የተጣራ ወርቅ ራሱ ብቻ እንደሚሆን ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ ቀላል የሆነው እንዱ ትርጉም ያልተወሳሰበ ማለት ነው።

ከላይ የተጠቀሰው መዝገበ ቃላት ምሳሌ አድርጎ የሚሰጠው በእጅ ያለን መሳሪያ ነው። እንዳንድ መሳሪያ ታዩትና ውስብስብ ሲልባችሁ ይሄ የተወሳሰበ ነው ትላላችሁ። ቀለል ያለውን ግን ማለትም ፈትታችሁት ወዲያውኑ ልትገጥሙት የምትችሉትን ቀላል መሳሪያ ነው ትሉታላችሁ። እንደዚያ ሊሆን ማለት ነው። ወይም ደግሞ በአለምሮ ውስጥ ተሰውሮ የተቀመጠ ተንኮል ከሌለበት ያንጊዜ ቀላል ነው እንለዋለን።

ህጻናት ቀለል ያለ ማንነት (ቀሊልነት) አላቸው የምንልበት ምክንያቱ ድብቅ የሆነ ተንኮል ነገር ለለሌላቸው ነው። በአማርኛ "ቅንነት" የምንለው ይህ ሐሳብ ግን እንደኛው ትርጉሙ ግልጽነት (Plainness) ነው። ለምሳሌ እንዳንድ ልብሶችን ሊይታችሁ ከሆነ ብዙ የተወሳሰበ ዲዛይን፣ ብዙ ሕብረ ቀለም የላቸውም። እሀቶቻችን ሊነጋገሩ ለፃታችኋቸው ከሆነ "እንቺ እኮ እንዲህ ዓይነት ቀለል ያለ ቀሚስ ስትለብሺ በጣም ያምርብሻል" ይባባሉ። ምን ማለታቸው ነው? ዲዛይኑ ውስብስብ ያልሆነ፣ ብዙ ዓይነት ቀለማት የሌሉት፣ ከጨርቁ በቀር ብረታ ብረት፣ ማለጌጫ ነገር የሌለው ማለታቸው ነው። በቃ እንድ ዓይነት ቀለም ያለው ቀለል፣ ጥርት ያለ ቀሚስ ነው፤ ያምራል ማለታቸው ነው።

ቀላል የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አውድ ከወሰድነው "ጤናማ" ማለት ነው። ጤናማ ትምህርት የሚለው ሐሳብ ያለው ቀሊልነት ውስጥ ነው። ግን ጥያቄ ልጠይቃቸሁ "ቀላል ነው ስትሉ ምን ማለታቸሁ ነው?" ወይም "እርሷ ቀለል ያለች ሴት ነች" ስንል ምን ማለታችን ነው? ቅን ሰው ናት ወይም ጮሌ ሊይደለችም ማለታችን ነው።

ዓለም የሚፈልገው አብሮት የሚሄደውን ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትርጉም ግን ኑሯችንን አናቅልል የሚል ነው። ዛሬ በጌታ ቃል የምላችሁ ያንን አይደለም። ቀላልነት የውስጥ የልብ እና የውጪ ነገር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ቆሮንቶስ መልዕክቱ ምዕራፍ 11፥3 ላይ *"ነገር ግን አባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፡ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ አፈራለሁ"* ይላል። በዚህ ክፍል ላይ ቅንነት የሚለውን ቃል እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ "ጤናማ" ብሎ ነው የሚሰው። ትርጉሙም "ንጹህ የሆነ" ማለት ነው። ይህም አባብ በተንኰሉ ገብቶ ንጹህ የሆነውን የሔዋንን ሐሳብ እንዳበላሸባት የእናንተንም ንጹህ የሆነውን ሐሳባችሁን እንዳይበላሽባችሁ አፈራለሁ ማለቱ ነው። ንጽህና ሰው በጎ እና መልካም የሆነውን ነገር የሚያስብበት በልቡ ውስጥ ያለ ነገር ነው።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ላይ እነዚህን ሰዎች እንዲት ድንግል ሴት ለወንድ እንደምትታጭ እኔም ለአንድ ወንድ ለክርስቶስ አጭቻችኋለሁ። ስለዚህ የሚያበላሻቸው ነገር እንዳይኖር ብዬ አፈራለሁ ሲል ምን ማለቱ ነው? ቅንነት ወይም ጤናማነት የሚገኘው የኢየሱስ በመሆን ላይ ብቻ ነው። በጌታ ላይ ትኩረት በማድረግ ብቻ ላይ ነው። ሙሽራው ሙሽሪትን ሊወስዳት በመጣ ጊዜ ተቀናቃኝ ወንድ ቢመጣበት ሚስቱን ሰዚያ ሰው አሳልፎ ለመስጠት የሚፈቅድ ማን ወንድ አለ? ማንም የለም። አንድ "የእኔ ብቻ ናት" የሚለው ነው ሊወስዳት የሚችለው። በመንፈሳዊ አነጋገር ሰው ለክርስቶስ ብቻ የሚሆነው፣ ሐሳቡ ቅን ሲሆን ብቻ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6፥22 ላይ *"የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ አንጻያህ ጤናማ ብትሆን፣ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፣ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል"* ብሎ በተናገረው ቃል ውስጥ "ጤናማ" የሚለው ቃል "ነጠላ" ተብሎ ነው የተጠቀሰው። በዚህ ክፍል አውድ መሠረት "ጤናማ" ማለት ነው። "ነጠላ" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የዘር ሐረጉ "ቀሊልነት" ከሚለው ቃል ጋር ይገናኛል። ምን ማለት ነው? ዓይናችን ሳይደበላልቅ አጥርቶ ንጹህ የሆነውን ነገር አይቶ እንደሚነግረን እንደዚሁ ሕይወታችንም ሳይደባልቅ፣ ሳይበርዝ ሌላ ሦስት ወይም አራት ነገሮችን ሳይጨምር በክርስቶስ ላይ ብቻ ትኩረት ቢያደርግ ሕይወታችን ቀላል ይሆናል ማለት ነው። ቀሊልነት የልብ፣ የውስጥ ነገር ነው።

ቀሊልነት በውጪም የሚታይ ነገር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ቆሮንቶስ መልዕክቱ ምዕራፍ 1፥12 ላይ ሲናገር *"ትምክህታችን ይህ ነውና፣ በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን፣ በአግዚአብሔር ቅድሰናና ቅንነት በዚህ ዓለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ እንደኖርን የሕሊናችን ምስክርነት ነው"* ይላል።

ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚናገረው በእናንተም ሆነ በአግዚአብሔር ፊት በቅድስና እና በቅንነት የኖርነው ቀላል ሕይወት ነው ትምክህታችን እያላቸው ነው። ሐዋርያው ለአንድ ዓመት ከመንፈቅ ያህል በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ሲኖር የዕለት ተዕለት ኑሮውን አቅልሎ ነበር የኖረው። በዚያ የኖረው ቀላል ሕይወት በየዕለቱ ተገልጦ የሚታይ ስለነበረ ኑሯችን የተሳለጠ ነው ብሎ ይናገራል። ይህንን ዓይነት ሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን! በማንም ሰው ላይ ሳይከብድ በእጅቹ እየሰራ "ኑሮዬ ይበቃኛል" ብሎ የኖረባቸውን ወራት እያሰበ እግዚአብሔርን እየመሰልን መኖሩ ከሁሉ ይበልጥብናል፤ ምንም ነገር ወደ አዚህ ዓለም አላመጣንምና ስንሄድም ምንም ይዘን አንሄድም። አንዳች ልንወስድም እንችልምና፤ ምግብ እና ልብስ ካለን ይበቃናል ብሎ በኖረው በዚያ ቀላል ኑሮ በአናንተ ፊት ተገለጥን፤" ብሎ ይናገራቸዋል።

ይህን ቃል ስንተረጉመው መፈታት፣ ነጻነት ያለበት፣ አለት ዕለት የሚገለጥ፣ ያልተወሳሰበ፣ ቀጥ ያለ፣ ተንኮል የሌለበት፣ ጤናማ፣ እና እንድ ነገር ላይ ያተኮረ ሕይወት ማለት ነው። ጌታስ እንዲህ ዓይኑን ሕይወት እንዴት ነው የኖረው? ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ የተወለደው በበረት፤ ያደገውም በአናጢ ቤት ውስጥ ሆኖ፣ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ እንደ ንጉሥ "ሆ!" አየተባለለትም ወደ ኢየሩሳሌም በመግባትም ነው የኖረው።

ኑሮን ከዚህ በላይ እንዴት ልታቀሉት ትችላላችሁ? ጌታ አኮ ኑሮን በጣም አቅልሎት ነው የመጣው። ወደዚህ ምድር ሰለ መምጣቱ ከዋከበት ሳይቀሩ የተናገሩለት እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ታላቅ ንጉሥ ሆኖ ሳለ በበረት ተወልዶ፣ በአናጢ ቤት ውስጥ አድጎ፣ በአህያ ላይ ተቀምጦ ከተላልቆቹ ጋር ሳይሆን ሃጢአተኛ ከተባሉ ሰዎች ጋር እየበላ እና እየጠጣ ነው የኖረው። እንድን ሰው ለማግኘት ብዙ መንገዶችን አቋርጦ የሄደ ሰው ነው። ከዚህ በላይ ኑሮን እንዴት ልናቀሰው እንችላለን? ከዚህስ በላይ በጣም ቀላል እና ወጪ የሌለበት ኑሮ ከየት ታመጣላችሁ? ጌታ ኑሮን በጣም አቅልሎት ነው የመጣው።

ትዝ ይላችኋል አንድ ጊዜ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ አንድ ሰው ወደ አርሱ ቀርቦ "ጌታ ሆይ ልከተልህ?" አለው። ጌታም ሲመልስለት *"ለወፎች ጎጆ፣ ለቀበሮዎችም ሚደረያ ጉድጓድ አላቸው፤ እኔ ግን ራሴን የማስጠጋበት ቤት የለኝም።* ትልቅ ቪላ ቤት የምታስብ ከሆነ ቁርጡን ልንገርህ፤ የለኝም እንደ ማለት ነው።

ጌታ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ዘመን ኑሮን በጣም አቅልሎት ነው የኖረው። አንደዚሁ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12፥13 ላይም አንድ ሰው ወደ አርሱ ቀርቦ "መምህር ሆይ ርስቱን ከእኔ ጋር አንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው አለው"። ጌታም "አንተ ሰው ፈራጅ እና አካፋይ በላያችሁ አንድሆን ማን ሾመኝ? አለው። ይህ ማለት በማይመለከተኝ ጉዳይ አልገባም ነው። ያ የእናንተ ጉዳይ ነው። እኔ ልሰራው የመጣሁበት ጉዳይ አለኝና አርሱን ነው የምሰራው።

አንደዚሁ ሌላ ጊዜ ደግሞ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ሰለ ገንዘብ ሲናገር ምን አላቸው? "ሰሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም" እና ምረጡ። ጌታ ኢየሱስ ኑሮ የቀለለት ለካስ በምርጫ ሰሰ ኖረው ነበር። ጌታ በዚህ ዓለም ላይ ንብረት ሰለ ማፍራት የወሰደው አቋምም ነበረው። አንድ ጊዜ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13 የመጨረሻው ራት ምሽት ላይ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበበት ስዓት ይሁዳ አሳልፎ ሲሰጠው ከመካከላቸው ብድግ ብሎ ወጣ። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ይሁዳ ሲወጣ ሲያዩት ግን ዕቃ ሊገዛ ወይም ሄደህ ለድሆች ስጥ ያለው መስሏቸው ነበር። ደቀ መዛሙርቱ እንዲያ እንዲያስቡ ያደረጋቸው ነገር ምንድነው? ጌታ ያለውን ለሌላቸው እያካፈለ ይኖር ስለነበር ነው።

ዓይን ማብራት እየቻለ፣ ዕድሜ እየጨመረላቸው፣ የሞተ እያሰነሳ እና ሌሎችንም ተዓምራትን እያደረገ ሁሉን በታምራት ማኖር ሲችል በጎንዘቡ ይሰራ እና ያሰግል የነበረበት ጊዜም ነበር። እናም "ለድሆች ሊሰጥ ነው" ብለው አሰቡ ይላል። አምን ሰዎች ካላቸው ነገር ቆርሰው ሲያካፍሉ ይቀላል አይደል? ማካፈል ይቀላል!

ጌታ ልክ መሰቀሱ ስር ሲደርስ የእርሱ ነው ተብሎ የሚወረስ ሀብት አልነበረውም። የአፍሪካ መሪዎች በቁጥር ስር ውለው ከሥልጣናቸው ሲወገዱ በብዙ ሚሊዮን ሽረ እንዲያውም በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሐብት ነው የሚወረስባቸው። ጌታ ግን ከለበሳት ልብሱ በቀር ሌላ ምንም ዓይነት ሀብት አልነበረውም። ያችኑም እጅ ጠባቡን የሮማ ወታደሮች ወስደው ዕጣ ተጣጥለውባታል። ማንም ሰው ሞት አፋፍ ላይ በሚደርስ ሰዓት ያለችውን ሀብት ሰቀሩት ቤተሰቡቹ ወይም ቤተ-ዘመዶቹ እንዲሰጥለት

ይሳነዘዘል። ጌታ ግን መሰቀል ላይ ሆኖ የሚናዘዘው ሁበት አልነበረውም። የተናዘዘው አንድ ነገር ቢኖር የእናቱን ነገር ነበር። እናቱን "እነሆ እናትህ" ብሎ ለዮሐንስ አደራ ሰጣቷት ነው የሄደው። የዚህን ዓለም ኑሮ ከዚህ በላይ እንዴት ቀላል ልናደርገው እንችላለን? ጌታ የዚህን ምድር ኑሮ በጣም አቅልሎት ነበር የኖረው።

ይሄንን ሐሳብ ያመጣሁት ለምንድነው? እግዚአብሔርን መምሰል የምንፈልግ ከሆነ ሊየሱስ የሄደበትን መንገድ መሄድና ያደረገውን ነገር ማድረግ ስላለብን ነው። እግዚአብሔርን መምሰል በአንድ ቀን የምንደርሰበት ግብ ሳይሆን በየዕለቱ የምንለማመደው ነገር ሰለሆነ፤ ዛሬ ይሄን ነገር መለማመድ ከጀመርን እግዚአብሔርን እየመሰልን እንሄዳለን። በነጻነት እንዳንኖር የሚያደርጉን ነገሮች ሕይወታችንን የሚያዋሳስቡ ነገሮች በመሆናቸው ቀለል ያለ ሕይወት ለመኖር በጣም ጓዝ ቀላሎች መሆን ያስፈልገናል።

እንደ ቤተሰብ ወይም ጓደኞሞች ከለዎች ጋር መንገድ እንሂድ ተባብለችሁ ሱትሄዱ እኮ መሄድ የምትፈልጉት ወደ አንድ መዳረሻ ነው የሚሆነው። የምትጓዙት ወደ አዲስ አበባ ሊሆን ይችላል። የምትበሩበት አውሮፕላን አንድ ነው፤ ነገር ግን እናንተን የሚያለያዩችሁ የያዛችሁት ጓዝ መጠን ነው። አንዳንዱ ሰው መንገድ ለመጓዝ ሲዘጋጅ ጓዙን አሳጥሮ፣ አሳንሶ፣ ቅልብጭ አድርጎ አሽጎ ሲወጣ፤ እንዳንዱ ደግሞ አራት ትላልቅ ሻንጣ በመያዝ ሸክሙን ያበዛል። እኛ የተጠራነው ግን ጓዝ ቀላሎች ሆነን አንድነኖር ነው።

እግዚአብሔር አባቶቻችንን የከነዓንን ምድር ወስዶ አሳይቷቸው ይህችን ምድር ለዘርህ አሰጣለሁ አያላቸው አንድ ጫማ የሚያክል መሬት ግን አልሰጣቸውም። ለአብርሃም አንድ ጫማ የምታክል መሬት ሳይሰጠው ግን ይሄ የዘርህ ነው እያለ ያለዋል። የዕብራውያን ፀሐፊ "ምንም ነገር ሳይወርሱ ድንኳናቸውን እየተከሉ እና እየነቀሉ ኖሩ" ይለናል። እኛ ደግሞ ከሁሉም የማንወደው ነገር ይሄ ድንኳን ትክሉ የሚለውን ነው። ድንኳን በቀላልነቱ ብቻ ነው የሚወደደው እንጂ ሌላ ምን ውበት አለው? ድንኳኑ የሚፈለገው ቀላሉን ኑሮ ለመኖር ብቻ ነው። እኛ ደግሞ ድንኳኑን አንወደውም። ከሆነልን መሠረቱን በብረትም፣ በአርማታም አጥብቀን እንዲሁም በሚያምር ድንጋይ አሳምረን መገንባት ነው የምንፈልገው።

አዚህ አሜሪካን አገር መጥታችሁ ቤት ሲሰሩ ካያችሁ የአገር ቤቱ ትዝ ቢላችሁ "ለካስ የጦር ሜዳ ምሽግ ነበር ስንሰራ የነበረው እንዴ!?" ነው የምትሉት:: ምክንያቱም በጣም አጥብቀነው በምጽዓቱ ቀን እንኳ እንዳይፈርስ አደርገን ነው የምንሰራው:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኑሮህን እቅልለው ነው የሚለን፤ ጓዝ ቀላሎች እንድንሆንም ነው የሚፈልግብንና ራሳችንን እንመርምር::

እህቶቻችን ከሚገለገሉበት እና በለስት ዓይን ከሚያዩት የግል ንብረታቸው እንዱ የሚያንጠለጥሉት ቦርሳቸው ነው:: ታዲያ ቦርሳቸውን ከሳንቲም እና ብር አንስቶ፣ ኩልን ጨምሮ እነስተኛ የፊት መስተዋት፣ እስከ የመኪና ቁልፍ እና የፊት ማበሻ ወረቀት፣ ሌላም፣ ሌላም የማያጭቁበት ነገር የለም:: በጊዜ ሂደት ቦርሳቸው ኑሮን የማቅለል ብልሃትን እንዲከተል ካላደረጉት እና በየጊዜው የሚሞጅሩበት ቁሳቁስ እየጨመረ ከሄደ፤ ቦርላው ቅልብጭ ያለ የሴት ወግ ማዕረግ ዕቃ መያዣ እና መገልገያ መሆኑ ቀርቶ የብሰጭት እና "ኡፍ ደግሞ!" የሚያስብል ምከንያት ሊሆን ይችላል:: እንዴት? ከዕለታት አንድ ቀን እንድ የቤት ወይም የመኪና ቁልፍ ቢጠፋ እና ቦርሳው ውስጥ ፍለጋ ቢጀምሩ ለፍለጋው የባሎች ልዩ ድጋፍ እና ርዳታ የሚጠየቅበት ቀን ደረሰ ማለት ነው::

ሕይወታችንንም ከዓይናችን ላይ ከለላውን እየከላን ብንመለከት እንዲሁ ነው:: "ያየሁት ነገር እይለፈኝ!፣ አማረኝ!፣ አሰኘኝ!" እያልን በየጊዜው ወደ ሕይወታችን ያሰገባነው ስንቱ ግሳንግስ፣ እንቶ ፈንቶ ጓዘ ብዙ እደረገን:: በገዛ ራሳችን ስንቱን ንትረን እንደ አልቅት እየተጣበቀብን፣ ደግ ነው ብለን ለሥጋችን ያመጣነው ለነፍሳችን ጠንቅ ሆኖ ተጣብቶን፤ ፍርጃ ሆኖብን የሌሎችን ወገኖች የጸሎት ተጋድሎ እሰከ መማጸን እድርሶን የለም እንዴ!?

እንደ ወታደር ቀጥ፣ ቆፍጠን ብለን መራመድ ያቃተን እኮ ጓዛችን ቅልብጭ አልል ብሎን ነውኮ:: ከከርስትና መርሆዎች አንዱ ጓዘ ቀላል መሆን ነው:: ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ "ተመልከት ዓላማህን፣ ተከተል አለቃህን" እንዳልነው የእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስ እንዲህ ጓዘ ቀላል ሆኖ ከኖረ እንደምን እርሱን ከመከተል ወደ ኋላ እንላለን?

በገላትያ 6፥17 ላይ "እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ ለእንድ ሰንኳ ላይድከመኝ" ብሎ የሚናገረው በጣም ኃይለኛ ቃል ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ የሚለው ስለ ስሙ

የደረሰበትን ስደት እና መከራ ነው:: ማህተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ የሚለው የተሸከመው መስቀል ሰውነቱ ላይ የሰራቸውን ምልክቶች ነው:: ሰለዚህ ማንም ሰው እንዲያደከመኝ ሌላ ሸክም እንዲጭንብኝ አልፈልግም:: አኔን ግድ የሚለኝ የኢየሱስ ክርስቶስ እና የትንሳኤውን ኃይል ማወቅ ነው:: ቢሆንልኝ ደግሞ በሞቱ እንኳን ልመሰለው ሁሉን ነገር እንደ ጉድፍ ቆጥሬዋለሁ:: የኋላዬን እየረሳሁ ወደ ፊት ሃምዘረጋው የምኖርለት እና የምሞትለት የከበረ ዐላማ ሰላለኝ ሌላ ሸክም ልሸከም አለፈልግም ነው የሚለን:: አማዚአብሔር እንዲህ ዓይነት የጨከነ ልብ ይስጠን:: በዚህ ምድር የምንኖረው ዕድሜ እኮ ለባ፤ ሰማንያ ዓመት ነው:: ይሄ በጣም ጥቂት ነው:: የምድሩን ኑሮ ከዘላለሙ ጋር ካወዳደርነው የሚያልፍ ነገር ነው:: ያዕቆብ እንደ እንፋሎት ነው፣ ኢሳይያስም እንደሚረግፍ አበባ ነው ብለውታል:: ታዲያ ይሄ የሚያልፍ ጊዜያዊ የሆነው ቀላሉ ነገር ሕይወታችንን ለምን ያከብድብናል?

ይህ የተፈታ፣ ነጻነት ያለበት፣ ያልተወሳሰበ፣ ቀጥ ያለ፣ ተንኮል የሌለበት፣ ጤናማ፣ እንድ ተኮር እና ዕለት ዕለት ልምምድ ያለበት ቀሊል ሕይወት እንዲኖረን በቅድሚያ ልንወሰዳቸው የሚገቡን ርምጃዎች አሉ:: እነዚህም:-

፩. <u>ቅደም ተከተል ይኑረን</u>

በኑሯችን መጀመሪያ መተግበር የሚኖርብን እንዱ ለነገሮች ቅደም ተከተል መሰጠትን ነው:: ይህ ማለት በኑሯችን እንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ብለን የምንለውና ቅደም ተከተል የምንሰጠው ነገር ሊኖረን ይገባል ማለት ነው:: ጉዳዮቻችንን በሙሉ በፈታችን አሰቀምጠን በእናንተ መካከል አላበላልጥም፤ ሁላችሁም ለእኔ እንደኛ ናችሁ ብንል ምንድነው የሚሆነው?

ሁሉንም እንደኛ ወይም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ማድረግ እንችልም:: በሕይወታችን ቅደም ተከተል ልንሰጣቸው የሚገቡን ነገሮች ሊኖሩን ይገባል:: ቅደም ተከተል የሌለው ሕይወት በጣም ምስኪን ነው:: እንደ የውሃ ላይ ኩበት ወዲህና ወዲያ እየዋለለ አንዱንም ሳያረካ እንደባዘነ ነው የሚኖረው:: ቅደም ተከተል ያስፈልገናል:: ሕይወቴን፤ ቁጭ ብዬ መዝኜ በዚህ መንገድ ነው የምመራው ያዋጣኛል ብዬ፤ ባልኩት ነገር ብመራው የማታ ማታ አልቆጭም::

ጉዳዮቼን እንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ ብዬ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ አለብኝ:: ነገሮቻችንን እንዲህ ማቀናበር እና ፈር ማስያዝ ካልቻልን ሁሉንም ነገር በአንድ

መቀጫ ውለጥ እየሞጀርን የምንወቅጥ ከሆነ፤ እኛም እንረካም፣ ዘመናችንም የእርካታ አይሆንም። ፍጻሜያችንም የብኩን ሰው ፍጻሜ ነው የሚሆነው። ስለዚህ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6፥33 ላይ ሲናገር *"አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ለሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል። ስለዚህ ለነገ በማሰብ አትጨነቁ፣ የነገ ሞንቃት ለነገ ይደር"* ይላል። ቀዳሚውን ነገር መጀመሪያ እናድርገው። ይሄ ትልቅ ጥበብ፣ ትልቅ እውቀትም ነው። ቅደም ተከተል በቤታችን ሊኖር ይገባል።

ቅደም ተከተሉ ሲኖረን ጊዜያችንን ለሚሻማ ለእንደኛው እንሰጠዋለን፤ ከዚያ ሲተርፍ ለሁለተኛው፤ ከእርሱም ከተረፈ ለሦስተኛው እንሰጠዋለን። ገንዘብ በእጄ ሲገባ ቅደም ተከተሉ ካለኝ "መጀመሪያ ለምንድነው የማወጣው?" ብዬ ራሴን አጠይቃለሁ። ቀጥዬም ለሁለተኛው፣ ቀጥሎም ለሦስተኛው በመሰጠት ሕይወቴን ሚዛናዊ ማድረግ እችላለሁ። ከግንኙነትም እንጻር ቢሆን ግንኙነቶቼን በቅደም ተከተል ውስጥ ማየት አለብኝ። ውጪ ለባልንጀሮቼ ይህ ቀረው የማልባል ሰው ሆኜ፤ በቤቴ ለሚሰቴ ናጩርት ብሆንባት ምንኛ ሞኝ ሰው ነኝ። አበው "የቤት ቀጋ የዱር አልጋ" እንዲሉ ማለት ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቅደም ተከተሉ ለለተዛባበት ቤቱን መጠለያ ብቻ አድርጎታል ማለት ነው። እንግዲያው አንድ ሰው ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለቤቱ፣ ለትዳሩ፣ ለቤተሰቡ፣ ለባልንጀራነቱ፣ ሰቃል ኪዳን ግንኙነቱ ከሆነ ቅድሚያ መስጠት ላለበት ነገር ቅድሚያ መለጠት አለበት። አንደ ቅደም ተከተሉ መሠረት ከሆነ መጀመሪያ የሚቀድመው የውጪ ባልንጀሮች ሳይሆኑ ሚስት ወይም ባል ነው። በሕይወቴ ቅደም ተከተል እንደሚያስፈልገኝ ሁሉ፤ እርሱንም እኔው ራሴ እንጂ ማንም ሰው አይሰራልኝም።

በልጅነቴ እናቴ በአንደኛ ደረጃ ይሄንን አድርግ፤ ሁለተኛ ይሄንን፣ ሦስተኛ ይሄንን እያለች አሳድጋኛለች። ሳድግ ደግሞ ቤት ውስጥ ትንሽ ራሴ ሞከሬው ሊሆን ይችላል። አሁን ግን ሙሉ ለው ነኝ። ወንጌል ሰምቼ ሕይወቴን ለክርስቶስ ከሰጠሁ እና በጌታ ከሆንኩ በኋላ ግን ቅደም ተከተሉን መስራት ያለብኝ እኔው ነኝ። አግዚአብሔር በሰጠኝ ዕድሜ፣ ገንዘብ እና ግንኙነቶች ምን እንደማረግባቸው በቅደም ተከተል የመጠቀሙ ነገር የእኔ ኃላፊነት ነው የሚሆነው።

ይገርማችኋል! በሕይወት ውስጥ ቅደም ተከተሉ ሲዛባ፣ ነገሮች የግርንቢጥ ሲሆኑ፣ ራስ እና ጅራት ቦታ ሲለዋወጡ፣ እንዴት ርምጃ ተወነካከሮ እንደሚደናቀፍ እና

በእሩጢም የመደፋት ያህል ምንኛ የከፋ እደጋ እንደሚያስከትል አንድ ምሳሌ ልስጥ።

እንዳንድ የግል ሚኒስትሪ ያላቸው እገልጋዮች፣ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ሠሄም ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ የድርጊት ትደም ተከተል መፋለስ ይገጥማቸውና፤ አሊያም እነርሱው ራሳቸው እንዳፈተታቸው ድንነት ከፈታቸው ከች ያለውን ያለ ቅደም ተከተሉ ሲከውኑ፤ ሦስት ድስት ጥዳ ቆላ እና ደጋ እንደምትረግጥ ሴት ከእንዱም ሳይሆኑ በከባድ ኪሳራ ነገራቸውን ይደመድማሉ። ከሌላ ሰው ይልቅ እነርሱን በምሳሌነት ላሳይ።

እንድ ሰው ጌታን ከተቀበለ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ጉበቶ በጌታ ነገር ማለትም በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያድግና ወደ አገልግሎት እርከን ይሸጋገራል። የአገልግሎት በር ያሰፋለታል፤ ፍሬው ይበዛል፤ እውቅናው ይጨምራል። የሚኒስትሪ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ሲገለጥ እብሮ ይዟቸው የሚመጣቸው ነገሮች ተራ በተራ እየወጡ በመካልከል ቁጥራቸው እየተመነደገ ይሄዳል። አገልግሎቱ እየሰፋ ተገልጋዮችም ቁጥራቸው እያሻቀበ ሲመጣ ሰውዬው እንደ ዓይኑ ብሌን የሚጠነቀቅለትን ይህን አገልግሎት "እኔ በአገልግሎቴ ፈጽሞ ቀልድ አላውቅምና፤ በእርሱ አትምጡብኝ!" ማለት ያጀምራል።

ሰው ሁሉ እጁን የኋሊት አጣምሮ አገልግሎቱን እንዲያከብርለት ይሻል። "ታዲያ ይሄ ምን ችግር አለው!?" ትሉኝ ይሆናል። ችግርማ በደንብ አለው። አግዚአብሔርም "እንዴ ምን ነካህ!? እገልግሎቱን አብረን አይደል እንዴ የጀመርነው? የሰጠሁህስ እኔ አይደለሁምን? እንዴት ነው እንዲህ እንደ ግል ንብረትህ ልትሳሳለት የጀመልከው? እንዲያው እንዴትስ የግል እንጡራ ሃብትህ ሆኖ ተሰማህ?" ሊለው ይጀምራል።

ሰውዬው አገልግሎቱን የራሱ ብቻ ስለሚያደርገው "መቼ በጸሎት ፊቴን ፈልገህ ታውቃለህ? ለብቻህ ሆነን እኔን መፈለግንስ ለምን አቆምክ?" ለሚለው ነአግዚአብሔር ጥያቄ የዝሆን ጆሮ ይሰጠኝ ይላል። ምናልባትም ይህ ሰው ቅድሚያ ነሚሰጠው ለአገልግሎቱ ብቻ ስለሆነ በቤቱ ውስጥ ከባለቤቱ ጋር ዓይን እና ናጫ ከሆነ ከረምረም ብሎም ይሆናል። ደግሞ ልጆቹስ! ፈጽሞ ለእነርሱ ጊዜ እልነበረውምና ረድቶዋል። ቅድሚያ የጌታ ሥራ በሚል ፍልስፍና እግር ተወርች ታስሮ ቤተሰቦቹን ዘንግቷቸዋል። የደባል ዓይነት ኖሮ።

ሚስት የባሏ ጠረን፣ ጨዋታው እና ቀልዱ ርቆባት፤ ልጆችም የአቢታቸው ናፍቆት ሆዳቸውን አያብስከሰከው፤ ሊያዩት፣ አብረውት ሊላፉት፣ እና ሊጫወቱ አየፈለጉ፣ የአጆቹ መደባበስ አያማራቸው ግና አባታቸው የሩቅ ሰው ሆኖባቸዋል። . .ቢቃ ምን አሰፋችሁ ይህ ሰው ቤተሰቦቹም ተቸግረውበታል።

የማታ ማታ ይህ አገልጋይ ከቤቱ አየራቀ፣ አየራቀ ሄዶ ከሴላ ሴት ጋር አንሰላ በመጋፈፍ ሃጢአት ውስጥ መውደቅ ይጀምራል። ከዚያም "አገልጋይ አገሌ አኮ በዝሙት ሃጢአት ወደቀ!" ይባላል። ምድርም ቁና ትሆናለች። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም አማባብ ያላቸው ሰዎች "ከትዳር ጓደኛህ ውጪ በመሄድ በዝሙት ኃጢአት ወድቀሃልና ንስሐ ግባ" ይሉታል። እርሱም ንስሐ ይገባል።

ይቀጥሉና "እንግዲህ ንስሐ መግባትህ ደግ ነገር ነው፤ ግና አንደገና መንፈሳዊ ጣዕሙ መጥቶልህ ታገግም ዘንድ፤ ተስተካከለህ፣ ተመከረህ፣ እና ታርመህ ትወጣ ዘንድም ጥቂት ጊዜ ተቀመጥ፤ አገልግሎቱንም አቁም!" ሲባል ግን "አይ! አገልግሎቱማ የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም አንዴ! አንዴት አቆማለሁ?" ይላል።

አያችሁ! ይህ ሰው እንዲህ የሚሰው በቅደም ተከተል ጉዳይ ላይ የተዛባ አመለካከት ስላለው ነው።

ቅደም ተከተሉ ላይ እንደኛ መሆን ያለበት የትኛው ነው? አገልግሎቱ ወይንስ መንፈሳዊ ሕይወቱ? ታውቃላችሁ በሕይወታችን መንፈሳዊ ነገሮች እንደኛ ይሁኑ ሁለተኛ ማንም ሰው ስለ አናንተ አይወስንላችሁም። ቁጭ ብላችሁ መወሰን ያለባችሁ አናንተው ናችሁ። አኔም ለአኔ ቁጭ ብዬ መወሰን አለብኝ።

ከአግዚአብሔር፣ ከቤተሰቤ፣ ከቤቶ ከርስቲያን አገልግሎቱ፣ ወይም ደግሞ ከፖንዘቤ ይሁን ከንግዴ ወይም ከትምህርቴ ማን ቅዳሚ እንደሚሆን በሕይወቴ ቅደም ተከተል የማወጣው እኔ ነኝ። ከዚህ ምርጫችሁ በኋላ ኑሮ ይቀልላችኋል። እንድ የአማርኛ ተረት ልተርትላችሁ። "የባዳ ሞኝ ከዘመድ አኩል አርጉኝ" ይላል። ይህ ምን ማለት ነው? ይህ ሰው ቅደም ተከተሉን አያውቀውም ማለት ነው። አንዱ ሰው በአንግድነት ቤታችሁ መጥቶ "አንደ ልጅህ አድርገኝ" ቢል ይሄ ምን ማለት ነው? አናንተ ደግሞ በቤተሰቡ ሕግ ቅደም ተከተል አላችሁ። ቀዳሚው የቤተሰብ አባል፤ ከዚያ ደግሞ የሥጋ ዘመዶች፣. . እያለ ይሄድና መጨረሻ ላይ ባዳ ነው። ቅደም ተከተሉ ይሄ ነው።

በቃሉ መሠረት ቅድመ ተከተሉ እንደኛ እግዚአብሔር ነው። ከእኔ ሐሳብ ጋር ከተሰማማችሁ ከአግዚአብሔር ቀጥሎ ደግሞ ሁለተኛው ቤተሰብ ነው። ሦስተኛው እና አራተኛው ላይ ግን የተለያየ ምርጫ ሊኖረን ይችላል።

2. <u>ዓላማ ይኑረን</u>

ኑሯችንን የምናቀልበት ሁለተኛው መንገድ በዐላማ መመላለስ ነው። የምንሄድበትን እንወቅ። በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ መናገር የምፈልገው ዐላማ መር ስለሆነ ሕይወት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ ቆሮንቶስ መልዕክቱ ምዕራፍ 9፥25-26 ላይ ምሳሌ ሲሰጥ "የሚታገል ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፤ እኛ ግን የማይጠፋውን። ስለዚህ እኔ ሰው ያለ ሐሳብ አንደሚሮጥ እንዲሁ አልሮጥም፤ ዝም ብዬም ንፋስ እንደሚጎስም አልጎስምም" ይላል። ምን ማለቱ ነው? "ንጹህ የሆነ፣ ጥርት ያለ አእምሮ (ዐላማ) አለኝ፤ ወዴት እንደምሄድ አውቄ ነው በዐላማ የምሄደው። ደግሞም አቅጣጫዬን ይገፍ የምሮጠው" ይላል።

የበከሰ ወይንም የነጻ ትግል ስፖርት ውድድር ስታዩ ተወዳዳሪው ሰው መጀመሪያ ማወቅ ያለበት አስፈላጊ ነገር አለ። በከሰኛ ከሆነ ግልጽ ቡጢ ማሳረፍ ነው ያለበት እንጂ፤ "ሙቼም ጠላቴ ከዙሪያዬ አይጠፋም" ብሎ በማሰብ እንዲሁ በአቦ ሰጡኝ አጁን ቢያወናጭፍ ምንድነው የሚሆነው? ተጋጣሚው ዝም ብሎ ነው የሚያየው። ከዚያም እንዲሁ ሲወራጭ ሲወራጭ ውሎ መጨረሻ ላይ ይደክመዋል። ከዚያ በኋላማ አርሱን አያርገኝ ነው።

ወገኖቼ ሆይ! የምንሄድበትን ማወቅ ይኖብናል። እግዚአብሔር አሁን ስድሳ ዓመት ዕድሜ ሰጥቶኛል፤ ሰባም፣ ሰማንያም ዓመት እኖር ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ አንበል። በዚህ በሰጠኝ አድሜ ወዴት ነው የምሄድበት፣ ምንስ ነው የማደርግበት? አንዳንድ ጊዜ ውሳኔያችንን በደንብ ካየነው በሕይወታችን ጀምረናቸው ያልጨረስናቸው ነገሮች ብዙ ናቸው። ሁልጊዜ በሕይወታችን የምንሄድበትን መንገድ አቅጣጫ አውቀን ለዚያ ነገር የምንሥራ ከሆነ ወዳሰብነው ቦታ እንደርሳለን። የምንሄድበትን አውቀን ከጌታ ጋር አርግጠኛ ርምጃ መሄድ እስከቻልን ድረስ ሁሉ ነገር ይደረስበታል። ነገር ግን ዐላማ ይኑረን፣ የምንሄድበትን እንወቅ፣ ግልጽ የሆነ ግብ ይኑረን።

ሰዎች ታሪኩ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8፥22-26 ላይ የተጠቀሰውን ዐይነ ስውር ሰውዬ ወደ ጌታ አመጡትና ይዳስሰው ዘንድ ለመኑት። ጌታም በዐይኑ ላይ ተፋበት፤ እጁንም ጫነበትና አንዳች ታያለህን? ሲል ጠየቀው፤ ዐይነ ስውሩም "ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ" አለው። ይህን ሰው ግራ ያጋባው ነገር ምንድነው? እንደኛው ነገር ሰው እና ዛፍ ተቀላቅሎበታል። ሁለተኛው ያግሞ ዛፍ ይወዘወዛል እንጂ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ አይመላለስም። ዛፉ ከተመላለሰ ግን ችግሩ የግራ መጋባት ስለሚሆን ግልጽ አይታ ያስፈልገዋል። በሕይወታችን የሚታይ፣ ግልጽ የሆነ ነገር መኖር አለበት። እንዲያውም ግልጽ የሆነ ዕይታን አስከናኘ ድረስ ብዙ ጊዜያችንን ማጥፋት ያለብን ከጌታ እና አማዚአብሔራዊ ምክር ከሚመክሩን ሰዎች ጋር መሆን አለበት። ግብ ካለን ግልጽ ዕይታው ከዚያ በኋላ የሚመጣ ይሆናል።

3. <u>አምቢ ማለትን</u>

ኦሮን የምናቀልበት ሦስተኛው ዘዴ አምቢ ማለት ነው። ደግሜ አለዋለሁ አምቢ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ኑሮ ከባድ የሚሆንብን አምቢ ማለት የሚገቡን ጉዳዮችን አምቢ ማለት አለመቻላችን ነው። በቃ እኔ እኮ አምቢ ማለት ስለማልችል እንዲያው እንዳላሳፍረው፣ እንዳላሳፍራት ብዬ ነው እንላለን። ውጤቱ ግን ብዙ ነገራችን ተመሰቃቅሎ፣ ጸጋችን ተገፎ፣ ትግዕስታችን አልቆ፣ አፋችን ቆሽሾ፣ ልብሶችንን ጨርሰን ብዙ ምስቅልቅል ነገር ውስጥ መዘፈቅና መዳከር ነው። ከዚያ ነገር ውስጥ የምንወጣው ከሰድስት እና ከሰባት ወራት በኋላ ነው።

በዕብራውያን 12፥1-2 ላይ "... *ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፥ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ። የእምነታችን ፈጻሚና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት*" ይላል። እንኳንስ ክፉ ነገር ይቅርና ጥሩ ነገር ሆኖ እንኳን ከዐላማችን ጋር ካልሄደ እና ወደ ግባችን ካልወሰደን፣ እንደኛ ብለን ካስቀመጥነው ጥሩ ምርጫችን ጋር የማይሄድም ከሆነ ያንን ነገር እንኳን እምቢ ማለት ያስፈልገናል። ብዙ ጥሩ ነገሮች ቢኖሩም፤ እምቢ ማለት ግን አለብን።

ኦሮን ያካበደብን እግበስብስን የያዘነው ጥሩ የሆነ፣ ስናይ የመሰለ፣ ማራኪ የመሰለው ስንቱ ነገር ነው? አንዳንድ መልካም የሚመስሉ ነገሮች ሰውን ባሪያ አድርገው ያስራሉ፣ ሱስ ይሆናሉ። መልካም የሚመስሉ ነገር ግን ልማድ ወይም ሱስ ሆነውብን እነርሱን ስናጣ ቅር የሚሉንን ከእነርሱ መከልከል ጥሩ ነው። እምቢ ለማለት ደግሞ

ኃይል ያስፈልገናል።

4. <u>መልካምን በማድረግ፣ ያለንን ከሌሎች ጋር መካፈልን</u>

ኑሮን ቀላል የሚያረግልን የመጨረሻው ሐሳቤ በዕብራውያን 13፥16 ላይ የሚገኘውና "*. . ደግሞም መልካምን ማድረግን እና ያላችሁንም ከሌሎች መካፈልን ለትረሱ*" የሚለው ቃል ነው። ሕይወታችንን ቀላል ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ መልካምን ማድረግ እና ያሉንን ነገሮች ለሌሎች ማካፈል ነው። የብዙዎቻችን ሕይወት ታሰሮ ያለው የሕይወታችን እሽከርካሪት በእኔነት ላይ ብቻ ያጠነጠነ ስለሆነ ነው። ገንዘቡ፣ ጓደኝነቱ፣ እውቀቱ እና ሌላውም ነገር ሁሉ በእኔ ዙሪያ እንዲዞር የምፈልግ፣ በእኔ ዙሪያ እንዲዞር የማደርግ ከሆነ ቢቃ ከጌታ ነገር እየወጣሁ ነው የምሄደው። ወደ ጌታ እየቀረብኩ እንድሄድ የምፈልግ ከሆነ ግን እኔነትን ማቆም አለብኝ። እግዚአብሔር የሰጠኝ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ሌሎችም ነገሮች በሙሉ ለሌሎች ማካፈል፣ ሌሎችን ማገልገል የምችልበት አድርጌ መልቀቅ፣ መስጠት ብችል ኑሮ እየቀለለልኝ ይመጣል። ኑሮዬን በጣም የሚያከብደው ነገር መስጠትን ትቼ ማጠራቀሙን ስጀምር ነው። የራሴ እና የእኔ አድርጌ ስይዘው ነው።

በአንድ ወቅት አንድ ሰው ደንብኛ ወደሆኑበት ባንክ ሄደው ወደ ውሰጥ እንደ ገቡ "እንዴት አደራችሁ?" ሲሉ ሰላምታቸውን አቀረቡ። ሰላምታ መስጠታቸው ባልከፋ። ማና ሰውዬው ሰላምታ የሰጡት እዚያ ላሉት ሰዎች ሳይሆን እዚያ ባንክ ውጥ ላስቀመጧቸው ብሮቻቸው ነበር። እንግዲህ የእኚህ ሰው ልብ ሃያ አራት ሰዓት የት እንዳለ እናንተ ታውቃላችሁ። "እንዴት አደራችሁ?" እያሉ ለብር ሰላምታ አስከሰጡ ድረስ።

ለሌሎች ሰዎች መልቀቅ፣ መስጠት፣ ዕረፍት ማምጣት ስንጀምር ኑሮ በጣም እየቀለለን ነው የሚመጣው። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 17፥4 ላይ በአትከልቱ ቦታ በጸለየው ረዥም ጸሎቱ "*አባት ሆይ የሰጠሽኝን ሥራ በመፈጸም በምድር ለከበርኩህ*" ብሎ ነበር። ይሄ እንዴት ያለ ጸሎት ነው!! ጌታ በምድር የኖረውን ሰላሳ ሦስት ዓመት ተኩሱን አሰራው ዘንድ የሰጠሽኝን ሥራ ጥንቅቅ አድርጌ ጨርሻለሁ ብሎ አባቱ የሰጠውን መልሶ አስረከቦታል።

ወደ መስቀል ወስደው ሲሰቅሉት "ተፈጸመ!" በማለት ሥራውን አጠናቋል። እኛ በለማንያ ዓመት አላልቅ ያለንን ሥራ እርሱ በስላሳ ሦስት ዓመት ተኩል ጨርሻለሁ ማለት የቻለው ኦሮን አቅልሎ ስለያዘው ነው። ጊዜውን፣ ገንዘቡን፣ ጉልበቱን በሙሉ አባቱ የሰጠውን ሥራ ለመሥራት ቅደም ተከተል አበጅቶለት፣ "ምግብ ብላ እንጂ" ሲሉት፤ "አኔ የምበላው ምግብ አለኝ፤ የአናንተ አያስፈልየኝም" አያለ፣ ለሌሎች መልካም አያደረገ አና ያለውንም ሌሎችን ለመጥቀም አያካፈለ በመኖር ጥንቅቅ አድርጎ ነው የጨረሰው።

እኛም ይህን ማድረግ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን!!

ምዕራፍ 5

አገልጋይ ሁኑ!

ምዕራፍ አምስት

አገልጋይ ሁኑ!

ቀደም ባሉት አራት ምዕራፎች ላይ አግዚአብሔርን መምሰል ማለት ኢየሱስን መምሰል እንደሆነ፤ ይህ ደግሞ አርሱ ያለውን ማለት፣ ያደረገውን ማድረግ፣ አርሱ ያዘውተረውን ማዘውተር መሆኑን ተመልከተናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን አንድ ነገር ብቻ በማየት እና ያንን ነገር ብቻ በማድረግ ኢየሱስን መምሰል አንችልም። ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሳለ ኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ መስቀል ተሸክሞ ከሊቀ ካህኑ ቀያፋ ቤት እስከ ቀራንዮ ድረስ ሄዷል የሚለውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ከፍል በመውሰድ በየዓመቱ ኢየሩሳሌም እዮተመላለስኩ አርሱ የረገጠውን እያንዳንዱን መንገድ እየረገጥኩ ስለሄድኩ ኢየሱስን አልመሰለውም። ምክንያቱም ከምድር ሕይወቱ አንድ ነገር ብቻ ገንጥዬ ስለወሰድኩ ሁሉን ምሰል ስለማይከስት ነው።

ነገር ግን የጌታን ሙሉ ሕይወት ወስጀ፤ ይናገር፣ ያዘውትር የነበረውን፣ በአርሱ ሕይወት ውስጥ አርሱ የማይለውጠው፣ የማይጥለው፣ የሚደጋግመው ዋና የሆነው ነገር ምን ነበር? ብዬ ያንን ዋናውን ቁም ነገር በመውሰድ ሙሉ ሕይወቱን ልመስለው ብቱ፣ ብለማመድ ያ ነው ኢየሱስን ወደ መምሰል የሚያመጣኝ። አግዚአብሔርን መምሰል ማለት ያ ነው።

ለምንኖርባት ዓለም በጣም እንግዳ ነገር አየሆነ የመጣ ሐሳብ አግዚአብሔርን መምሰል ነው። ስው አገልጋይ መሪ መሆንን ፈልጎ ሁሉቱን አጣምሬ አይዛለሁ ብሎ ቢታገል ሰዎች ይሰቁበታል። እነዚህ ሁለት የሚታረቁ ነገሮች ናቸው። ብሎ በማያምን ወይም በማይቀበል ዘመን እና ትውልድ መካከል ነው የምንኖረው።

እንዲያውም አገልጋይ የሚለው ቃል ከተወሰነ የሥራ ዓይነት፣ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር፣ ከተወሰነ ዘመን እና ቋንቋ ጋር የሚደመር እንጂ ጨርሶ ከሰው ሁለንተና ጋር

የሚያያዝ ሐሳብ አይደሰም ብለው የሚያስቡ ብዙዎች ናቸው። ሰዎች አገልጋይ ብለው የሂሳብ ሠራተኛ ለማለብ፣ አገልጋይ ብለው ሐኪም ለማለብ፣ አገልጋይ ብለው ወታደር ለማለብ አይመጣላቸውም። ይሁን እንጂ የአግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረን ግን አገልጋይነት ገንዘብን የምንሠራው እንድ ነገር ሳይሆን ሙሉ ሕይወት እንደሆነ ነው።

አንድ ሰሞን "ስውሩ አለቃ" (The undercovered Boss) የሚል አንድ ጥናታዊ ፊልም በቴሌቪዥን ይታይ ነበር። ምናልባትም ፊልሙን አይታችሁት ሊሆን ይችል። በዚያ ፊልም ውስጥ ከአንድ ኩባንያ የበላይ ኃላፊዎች መካከል እንደኛው ሁኔታዎች ተመቻችተውለት ማንም የበታች ሠራተኛ ሳያውቅ መልኩን ቀይሮ እንደ አንድ አዲስ ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ የበታች ሥራ ላይ ተቀጠረና ዝቅተኛ ሠራተኞች በሚሠሩበት ሥራ ቦታ ላይ ተመድቦ ይታያል። ይህ ሰው የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ ነበር።

ይህ ሰው ይህን ያደረገበት ዐላማው ምን ነበር? አንድ የበላይ ሠራተኛ ታች ዝቅተኛ የሥራ ደረጃ ወርዶ ሲሰራ ምን ይፈጠራል? የበታች ሠራተኞች የሥራ ውሎ፣ ኑሯቸውስ እንዴት ነው? ለሚለው ምላሽ ለማግኘት ነበር። አላይ ባለው ወንበር እና ታች ባለው ሥራ መካከል ያለው ልዩነትስ ምን ይመስላል? አላይ ያለው ሰው ወደ ታች ወርዶ ቢሠራ ምን ይመስላል? ሥራውንስ እንዴት ይሠራው ይሆን? ይህን ለማወቅ ነበር ጥናቱ። እታች ያለውን እውነታ ለማወቅ። በጣም የሚገርም ነገር ነው። የበላይ አለቆቹ ከለለምሯቸው በላይ ነው የሚሆንባቸው። እንደዚህ ሆነው ነው ታች ያሉት ሰዎች የሚኖሩት!? ማለት ይጀምራሉ። ምክንያቱም መሪነቱ እና አገልጋይነቱ እየተፋቁ ለለሰነበቱ ነው።

ሰው መሪ እየሆነ ሲሄድ ከሚመራው ሕዝብ በጣም እየራቀ ነው የሚሄደው። ደቀ መዛሙርቱም ይሄ ነገር ውስጣቸው የተቀመጠ ነገር ስለነበር አንድ ጊዜ ከእኛ መካከል ትልቁ ማን ነው? እየተባባሉ ተከራከረው ነበር። ከጌታ ፊት ዘወር ያሉት በእርሱ ፊት መከራከር ስለማይችሉ ይመስለኛል። ዘወር ብለውም ሁሉም ትልቅ ነው የሚሉትን የየራሳቸውን የተናገሩ ይመስለኛል። ማነው ትልቅ? የሚለው ሃሳብ ሁሉም ሰው ዘንድ ያለ እንደመሆኑ በእነርሱ ልፈርድ አልፈልግም። ነገር ግን ችግሩን ችግር የሚያደርገው ነገር የትልቅነት መለኪያው ሲጠፋ ነው። ትልቅ ዮተባለውን ቦታ ያስመኛቸውና ጥያቄ ውስጥ የከተታቸው የትልቅነቱን መለኪያ አገልጋይ መሆንን ሳይሆን ጥቅም ማግኘ፣

መገልገያ! ማድረጋቸው ነው። የትንሽኛው መለያ ደግሞ አገልጋይ መሆን ነው። ትልቅ ተብዬው በትንሹ ይገለገላል፤ አገልግሎት ያገኛል። እርሱ ምንም አይነካም። ስለዚህ ሰው ከትንሽነት ማለት ከአገልጋይነት ወደ ላይ በወጣ ቁጥር መሪ እየሆነ እንደሚወጣ የሚያስቡ ስለሆነ የትልቅነት መለኪያው ነበር ችግሩ። ጌታ ግን ምንድነው ያላቸው? የትልቅነት መለኪያው ያ አይደለም። በእህዛብ ዘንድ በማያምኑት ዘንድ እውነት ነው፤ መገልገያው ያ ነው። አለቆቻቸው ይሰለጥኑባቸዋል፤ የወደዱትን ያደርጉባቸዋል፤ ያስገብሯቸዋል። በእኛ በሐበሾች ዘንድ "ገና በመስከረም ሊሾም በሰኔ እቦቢው ይበዛል" የሚል ተረት አለ። ምክንያቱም የትልቅነቱ፣ ባለስልጣን የመሆን ነገሩ ከጥቅሙ ጋር ነው የሚመጣው።

ጌታ ግን "በእናንተ ዘንድ ግን እንደዚህ አይደለም። ከእናንተ ትልቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን። ከእናንተ ማንም ፊተኛ፣ ዋነኛ መሆን የሚወድ ቢኖር ያ ሰው የእናንተ ሁሉ ባርያ ይሁን" ነው ያለው። ይህ ነው የአገልጋይነት መለኪያው።

የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻህፍት የተጻፉበት የግሪኩ ቋንቋ "አገልጋይ" የሚለውን ቃል "ዲያኮኖስ" ወይም ደግሞ "ዲያኮኖስ" ብሎ ነው የሚጠራው። ትርጉሙን በዘመኑ ከነበረው የባርነት ስርዓት ጋር አያይዞ ነው የሚያቀርበው። እነዚህ ሁለቱ ቃላት ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች "አገልጋይ" የሚለውን ቃል የሚረዱት በገንዘብ እንደ ተገዛ ባርያ ነው። ይህ በገንዘብ የተገዛው ባሪያ ምን ማድረግ ነው የሚጠበቅበት? እንቅልፍ ካልተኛ በስተቀር ሁልጊዜ ዓይናቹ፣ ጆሮዎቹ ወደ ጌታው ናቸው። የጌታውን ፈቃድ ለማድረግ ንቁ ሆኖ ቆሞ የሚያድር ሰው ነው። በቃ የሚያገለግለው ጌታውን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቡም ልከ እንደዚሁ ነው። አገልጋይ የራሱ መብት የሌለው ሰው ነው።

ጌታውን የሚያገለግል፣ ሌላውን ሰው የሚጠቅም፣ አለኝ ብሎ የሚሰው መብት የሌለው ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ባርያ የሚለው ሰው መብቱን ለጌታው ለመገዛት ሰጥቶ የገባ በመሆኑ የራሱ መብት የሌለው ሰው ነው። ጌታ ኢየሱስ በህይወቱ ሆኖ ያሳየን አገልጋይነት ያንን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር በመሆን አግዚአብሔርን ለመምሰል የምንከተልበት መንገዳችን መሆኑን ለማጣራት እንዲረዳን የአገልጋይን እና የአገልግሎትን ልዩነት ትንሽ በጎረታው ጥሩ ነው።

አገልጋይ ሲኖር ደግሞ አገልግሎት አለ። እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንድነው ልዩነታቸው? ጌታ የጠራን አገልግሎት እንድናገለግል ነው? ወይስ አገልጋይ እንድንሆን ነው? እነዚህን ነገሮች ለያይቶ ማብራራቱ ይጠቅማል። አገልግሎት ትርጉሙ ለአግዚአብሔር ክብር እና ለሰው ልጆች ጥቅም እንዲሆን አግዚአብሔር በፊት ለፊታችን የሚሰጠን ማንኛውም ዕድል ነው። በሥራ ቦታ ይሁን፣ በቤተ ክርስቲያን ወይም በሌላ በየትም ቦታ አግዚአብሔር የሚከብርበት፣ ሰው የሚጠቀምበት የትኛውም እኛ ልናደርገው የምንችለው እድል አገልግሎት ነው። አግዚአብሔር ብቻ ይከብር ሰው ይጠቀምበት ዘንድ እንጂ አገልግሎት ሁሉንም ነገር ይጠቀልላል። ይሁንና እነዚህን ሥራዎች በመስራት ግን አገልጋይ አንሆንም። ምክንያቱም ሰዎች ከተለያየ ምክንያት የተነሳ እነዚህን ሥራዎች ስለሚሰሩ ሥራውን በመስራት አገልጋይ አይኮንም። በሰዎች ዘንድ መንፈሳዊ ሆኖ ለመታየት የሚፈልጉ ሰዎች ከዚህ ምኞት እና ፍላጎት የተነሳ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ ለመታየት አገልግሎትን ሊሰሩት ይችላሉ።

ታሪኩ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18፡11 ላይ የተጠቀሰው ፈሪሳዊ *"አግዚአብሔር ሆይ ለኔ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ቀማኛ፣ ለመጸኖ፣ ለመንዝራ፣ ይልቁንም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ባለመሆኔ ለመሰማንሃለሁ፤ በሳምንት ሁለት ጊዜ ለጾማለሁ፣ ከማንኛውም ሁሉ ለሰራት ለወጣለሁ"* እንዳለው ማለት ነው። ሰዎች አገልግሎትን በውስጡ አንዳች ትርፍ አገኝበት ይሆን ብለው በደንብ ሊሰሩት ይችላሉ። ነገር ግን ያ የሚሰሩት ሥራ ከትርፍ ጋር የሚያያዝ ስለሚሆን ጌታ አገልግሎት ነው ብሎ አለመቀበሉን አለመዋቃቸው ነው።

ጳውሎስ በ፩ ጢሞቴዎስ መልዕክቱ ምዕራፍ 4፡7 ላይ አግዚአብሔርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆንላቸው ሰዎች እንዳሉ ይናገራል። ለትርፍ የሚሰሩ ሰዎች አሉ፤ ይህንን ደግሞም ያንን ባያደርጉ የአግዚአብሔር ቁጣ፣ ፍርድ እንደሚመጣባቸው አድርገው ግዴታ ሆኖባቸው የሚሮጡ ሰዎችም አሉ። ከዚህ የተነሳ ሥራው ጥሩ ሆኖ እያለ ሥራውን ለመስራት የተነሱበት የውስጥ ፍላጎታቸው ልክ ስላልሆነ ብቻ ነገሩ ይበላሻል። እጅ በትከክል እየሰራ ልብ በትከክል ስለማይመታ አግዚአብሔር አገልግሎቱን አልቀበልም ይላል። ስለዚህ ይህ ሰው ሥራ ሰራ እንጂ አገልጋይ አልሆነም ማለት ነው። አገልጋይነት የልብ ጉዳይ ነው። አገልግሎት እንዴ የምንሰራው ሳይሆን ሁልጊዜ የምንመላለስበት የሕይወታችን መንገድ ነው። ዛሬ ሲሳካልን የምንገባበት፣ ሳይሳካልን ሲቀር የምንወጣበት ሳይሆን ሁልጊዜ የምንኖርበት የሕይወት ዘይቤ ነው። አግዚአብሔር

ከአገልጋይ ጋር የሚያያይዘው ልቡን ነው።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10÷38-41 ላይ የተጻፈው የአልዓዛር እህት የማርታን ታሪክ ታስታውሳላችሁ። ጌታ ኢየሱስ ወደ እነ ማርታ ቤት እንደገባ ማርታ ወደ ጓዳ ገብታ ጉድ፣ ጉድ ማለት ጀመረች። ማርያም ግን ሄዳ ከእግሩ ስር ተቀምጣ የጌታን ቃል መስማት ያዘች። ማርታ በጓዳ ማርያም ደግሞ በመሣር ተጠመዱ። የማርታ ሥራ ለመስራት ጉድ፣ ጉድ ማለት ምንም ችግር አልነበረውም። ችግሩ የመጣው መቼ ነው? የማርታ ልብ ሲከፈት እና ኢየሱስን *"ጌታ ሆይ አህቴ ሥራውን ለለኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? አንድታግዘኝ ንገራት አንጂ"* ባለችው ጊዜ ነው።

ጌታ ግን *"ማርታ፣ ማርታ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፣ ትዋከቢያለሽም የሚያስፈልገው ነገር ግን አንድ ብቻ ነው፣ማርያም እኮ የሚሻለውን ደርሻ መርጣለች፣ ይህም ከእርሷ ሊይወሰድባትም"* ነበር ያላት። አገልጋይነት የልብ ጉዳይ እንጂ የሥራ ጉዳይ ብቻ ስላይደለ ትኩረት ማድረግ የሚኖርብን በልብ ላይ ነው ማለት ነው።

እንዲት ዕድሜአቸው የገፋ ፈረንጅ እናት አሁድ ቀን ለአምልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ከቤታቸው በመኪና ይመጡና እንደ ደረሱ እግራቸውን ማዘዝ ይቸግራቸው ስለነበር ከመኪና ለመውረድ በጣም ብዙ ደቂቃ ይወስድባቸዋል። ከዚያም እግራቸውን በመኪራ እየጎተቱ በጣም አዝግመው በመሄድ ከረጅም ትግል በኋላ የሚቀመጡበት ቦታ ደርሰው ይቀመጣሉ። በየሳምንቱ ለረዥም ጊዜ ይሄንን ያደርጋሉ፤ አናም አንድ ጊዜ ሰርክ ይከታተላቸው የነበረ አንድ ሰው የሴትዬዋ የሕይወት መሰጠት በጣም ስላስደነቀው ጠጋ ብሎ ሴትዬዋን "እሜቴ እርስዎ በየሳምንቱ ከመኪና ወርደው እዚህ ወንበር ጋ ደርሰው ለመቀመጥ እግርዎን እየጎተቱ እንዲህ ባለ ስቃይ እንዴት ይችሉታል?" ሲል ጠየቃቸው። ሴትዬዋም "እይ ልጅ! አግሬ ነው ዘግይቶ የሚቀመጠው እንጂ መጀመሪያማ ቀድሞ የደረሰው እኮ ልቤ ነው" ብለው መለሱት። አግዚአብሔር ይርዳን! መጀመሪያ ልብ ሲቀድም አግር የቱንም ያህል ቢጎተት ይደረሳል። አግዚአብሔር የልብ አምላክ ስለሆነ በእርሱ ፊት ዋጋ ያለው ልብ ነው። አግዚአብሔር ልብን ነው የሚያየው። አገልጋይነት የእጅ ሥራ ነገር ብቻ ሳይሆን የልብም ጉዳይ ነው። አገልጋይነት ስላገኘን ስላላገኘን፣ ስለተሳካልን ስላልተሳካልን፣ ስለሆነልን ስላልሆነልን የምንይዘው ሳይሆን እድሜ ዘመናችንን በሙሉ በልባችን ውስጥ ይዘነው የምንመላለስበት ከማንነታችን ጋር የምናያይዘው የእኗኗር ዘይቤ ነው።

ታሪኩ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10÷25 ላይ የተጠቀሰው የደጉ ሳምራዊ ታሪክ ትዝ ይላችኋል? ያ ሕግ አዋቂ *"መምህር ሆይ የዘለለም ህይወት ለመውረስ ምን ላድርግ አለው።* ኢየሱስም፦ *"በሕግ የተጻፈው ምንድነው? እንዴትስ ታነበዋለህ?"* ሲል መለሰለት። ሰውዬውም መልሶ፦ *"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ኃይልህ፣ በፍጹም ሃሳብህ ውደድ። ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ ይላል"* አለው። ከዚያም ጸሐፊው ሉቃስ ሰውዬው ራሱን ሊያጸድቅ ፈልጎ "ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?" አለው ይለናል። ይሄ ትልቅ ጥያቄ ነው። ሕግ አዋቂው አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትሰረቅ፤. . .ያሚሉትን እና ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ ሕጎችን ሁሉ ጠብቋል። በማህበረሰቡ መካከል ተቀባይነት ያለው ይህ ሰው ራሱን ለማጽደቅ ፈልጎ ጓደኞቹን እና እኩዮቹን ለማወቅ ባልንጀራዬ ማነው? ብሎ ጠየቀ። ከዚያም ጌታ ሰለ ደጉ ሳምራዊ፣ ሕግን ጠንቅቁ በመጠበቅ ነው የምኖረው ስለሚለው ፈሪሳዊ እና ስለ ካህኑ ታሪክ ነገረውና "ለዚህ ሳምራዊ ወገን ቸርነት ያደረገለት ማነው?" ሲል ጠየቀው። ይሄ በጣም የሚገርመኝ ታሪክ ነው። ምክንያቱም "ባልጀራዬ ማነው?" ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ጌታ ግን የመለሰለት "እንተ የማን ባልንጀራ ነህ?" የሚል ዓይነት መልስ በመሆኑ ነው። ከዚያም ምሳሌውን ነገረውና "ለመሆኑ ለዚያ በወንበዴዎች ተደብድቦ ለተጎዳው ለው ባልንጀራው ማን ነው?" አለው። "ከወደቀበት ስፍራ ያነሳው፣ ዘይት የቀባው፣ በአህያው ላይ ያስቀመጠው፣ ዋጋ በማውጣት ቸርነት ያደረገለት እርሱ ነው" አለው። ጌታም "አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ" አለው።

በዚህ ዓለም ላይ ሁሉም ሰው የሚጠብቀው ሰዎች ጓደኛ እንዲሆኑለት ነው። ብዙ ሰዎች ጓደኛ የሚሆኑትና የሚከቡት በምድራዊ ነገር የተባረከ ነው ተብሎ የሚታየውን ሰው ነው። ጌታ ግን የሚፈልገው ሄደን የእኛ ጓደኛነት ለሚያስፈልገው ሰው ጓደኛው እንድንሆን ነው። በዚህ ዘመን ይሄ በጣም ተግዳሮት የበዛበት እውነት ነው። ሕግ አዋቂውን ሰው የተሟጉተው የአገልጋይነት ልብ ጉዳይ ነው። ካህኑ እና ሌዋዊው ገለል ብለው የሄዱት እኮ አገልግሎት ስለነበራቸው ይሆን ይሆናል። ሌዋዊው የመዝሙር ጥናት፣ ካህኑ ደግሞ ከመዝሙሩ አገልግሎት በኋላ ወንጌል ሰባኪ እርሱ ስለነበረ ይሆን ይሆናል። ስለዚህ ሁለቱም በዚያን ዕለት ቦፐሮግራም የሚሰራ ሥራ ወይም አገልግሎት ስለነበራቸው ወደዚያ ሄዱ። ጌታ ግን በምሳሌው ውስጥ ለሕግ አዋቂው ሰው ያሳየው እውነታ አገልግሎት ሰለ ማገልገል ሳይሆን ሰለ አገልጋይነት ነበር። ምሳሌው አገልግሎት የልብ ጉዳይ ነው የሚል ነው።

ሁሉ ነገር ከውስጥ ማንነታችን ጋር የተያያዘ ስለሆነ አመለካከታችንን ትንሽ ግስተካከል ይኖርብናል። አገልግሎት ክርስቶስን ለመምሰል በአገልግሎት እንጠመድ ብለን በእጃችን የምንሰራው ነገር አይደለም። መቅደም ያለበት ልብ ነው። ጌታ የሚፈልገው በልብ አገልጋይነት እንድናገለግል ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው አገልጋይ እንድንባል ሳይሆን አገልጋይ ሆነን እንድንገኝ ነው። ለዚህ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን በሉቃስ 22÷27 ላይ *"ለመሆኑ፣ በማዕድ ከተቀመጠና ቆሞ ከሚያስተናግድ ማን ይበልጣል? በማዕድ የተቀመጠው ላይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ ያለሁት እንደ ለንድ አገልጋይ ነው"* ያለን ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው። በባህላችን ድግስ ላይ እንደ ትልቅ የሚቆጠሩት ድግሱ ላይ የተቀመጡት ሰዎች እንጂ ቆመው እነርሱን የሚያስተናግዱት አስተናጋጆች አይደሉም።

በሰው ዘንድ ያለው የታላቅነት መለኪያው ተቀምጦ መስተናገድ ነው። ጌታ "ማነው ትልቁ?" ካላቸው በኋላ መልሱን አስኪሰጡት አልጠበቀም። ወዲያው "የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ ሳለሁ እንደሚያገለግለው ሰው ነኝ" አላቸው። እግዚአብሔርን የምንመስልበት የአገልጋይነት ህይወት ወይም ኑሮ አንዱ መንገድ ይሄ ነው። እኔ በግሌ መመላለስ የምፈልግበት መንገዴ ይሄ ነው። አንባቢዎቼም እንዲመላለሱት የምፈልገው ይሄንን ነው። ለአገልግሎት የሚሮጡ ሰዎች ይህንን መልካም ምሳሌነት ያለውን ሕይወት "መምህር ነው፤ ነገር ግን የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጥባል፤ መሪ ነው፤ ነገር ግን የሁሉ ኋላ ሆኖ ይመላለሳል። እንዴት ያለ የሚጋጭ ሕይወት ነው" ይሉታል። በምድራዊ አተያይ ካየነው መሪነት፣ መምህርነት ትልቅነት ነው፤ በእግዚአብሔር አተያይ ግን ባርያነት ወይም የሁሉ አገልጋይነት ነው። እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ይክፈትልን!

እግዚአብሔርን መምሰል የምንችልበት መንገድ ኢየሱስ ከርስቶስ የመረጠውን የአገልጋይነት ሕይወት በመከተል ነው። ይሄንን በግልጽ የሚያስረዳልን የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍል የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13÷1-17 *"ጊዜው ልክ ክፋሲካ በዓል በፊት ነበረ፤ ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ ወደ አብ የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ አወቀ። በዓለም የነበሩትን የራሱ የሆኑትን ወደዳቸው፤ በፍጹም ፍቅሩም ወደዳቸው። እራትም ቀርቦ ሳለ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ዲያብሎስ የስምዖንን ልጅ የአስቆሮቱን ይሁዳ ልብ እነሳስቶ ነበር። ኢየሱስም አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ስር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔርም እንደ ተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ አውቆ ከራት ተነሳ፣ መጎናጸፊያውንም*

አስቀመጠ፤ ወዙንም በፎጣ ታጠቀ። ከዚያም በመታጠቂያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ ያብስ ጀመር።

ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ ጴጥሮስም፦ "ጌታ ሆይ፥ አንተ እግሬን ታጥባለህ? አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ የማደርገውን አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውላለህ አለው። ጴጥሮስም፦ የለም፤ እግሬን ከቶ ኢታጥብም አለው። ኢየሱስም፦ ካላጠብሁህማ፥ ከእኔ ጋር ዕድል ፈንታ የለህም አለው። ስምዖን ጴጥሮስም፦ ጌታ ሆይ አንዲያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም፥ ራሴንም አጠበኝ አለው። ኢየሱስም፦ ገላውን የታጠበ ሰው የሚያስፈልገው እግሩን ብቻ መታጠብ ነው፤ የቀረው አካሉ ሁሉ ንጹሕ ነው። ሁላችሁ ባትሆኑ፥ እናንተ ንጹሐን አይደላችሁም ያለው አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ያውቅ ስለ ነበር ነው። እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም ልብሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው፦ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? አናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና። እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፥ አናንተ እንዲሁ ለርስ በአርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል። ምሳሌ ትቼላችኋለሁ። አውነት፥ አላችኋለሁ፤ ለገሌጋይ ከጌታው፥ መልዕክተኛም ከላከው አይበልጥም። እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አውቃችሁ ብትፈጽሙ ትባረክላችሁ" የሚለው ነው።

ጌታ ትቶልን የሄደው ምሳሌው "እኔ እንዳደረግሁላችሁ አናንተም እንዲሁ እንድታደርጉ" የሚል ነው። በዚያች ምሽት እዚያ ከፍል ውስጥ ምን ነበር የተካሄደው? በአይሁዳውያኑ ልማድ እግር የመተጣጠብ ስርዓት አለ። ግና በዚያን ቀን እነዚህ ደቀ መዛሙርት ዝም ብለው ወደ ከፍሉ ገብተው ተቀመጡ እንጂ በእንዳች በሆነ ምክንያት ሳይታጠቡ ሳይተጣጠቡ ቀርተዋል። ለምን ይሆን? ወንጌላዊው ይሀንን ስላልጻፈልን፤ እኔም እንዲህ ነው ብዬ አስረግጬ ልናገር አልችልም። ግን፣ . . .ግን በቤቱ ውስጥ እንዳች ድባብ የሰፈነ ይመስላል። ምን ዓይነት ድባብ? እንዴ፣ አይሁዳውያን ይህ የመተጣጠብ ስርዓት ካላቸው ብዙጊዜ ውሃው በዕቃ ተሞልቶ የሚቀመጠው ውጪ ነው። እንግዲህ ውሃው ይኖራል ማለት ነው። ግን ማን ቀድቶ ያቅርብ? ማበሻውንስ ማን ያምጣ? . . እቤታችሁ ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር ገጥሟችሁ አታውቁምን? አንድ የሚሠራ ሥራ ቤት ውስጥ እንዳለ ልበናችሁ እያወቀው ግን ማን ይስራው? እኔ ወይስ እርሱ? እርሷ ወይም ያኛው ብላችሁ አታውቁምን? . . ቢደቀ መዛሙርቱም መካከል የሆነው እንዲሁ ይሆንን?

ጌታ ተቀምጦ ሲያይ ቆየና ማበሻ ጭርቁን እና ሳህኑን ይዞ ተነሳ። ከዚያም እየሠረ የአያንዳንዳቸውን እግር አጠበ፤ እግሮቻቸውንም አበሰ።

ጴጥሮስ እና ጓደኞቹን አሰቧቸው። ይሄ ለእነርሱ ከአዕምሮ በላይ ነው። ምክንያቱም እነርሱ መምህር ብለው የተከተሉት እና ቦርሳውን ሊሸከሙለት፣ አሣሩን ሊያጥቡት፣ መኝታ ቤቱን ሊያስተካክሉለት፣ ወደሚልካቸው ቦታ ሊሄዱ፣ ከፊቱ ቀድመው በመሄድ እውፌ እንዳይበላው ሊያባርሩለት፣ እነርሱ ሞተው እርሱ በህይወት እንዲቆይ ሁሉን ነገር በእነርሱ ሊጠቀም ቃል የገቡለት ሰው አሁን የነበረውን ልማድ ሁሉ ገልብጦ እኔ እግራችሁን አጥባለሁ ብሎ ሲነሳ ግር አላቸው። ስለዚህም ጴጥሮስ ከሌሎቹ ቀደም ብሎ "አይ አንተ የእኔን እግር ልታጥብ አይገባህምና በፍጹም እታጠብኝም" አለው። ይህን ማለቱ አይፈረድበትም፤ ነገሩ የተገላቢጦሽ ስለሆነበት ነው። እርሱ የገባው እነርሱ የመምህራቸውን እግር እንደሚያጥቡ እንጂ፤ እርሱ እንደሚያጥባቸው አይደለም። እንዲህ አስበውት ስለማያውቁ "እንዴት ይሆናል?

ጌታ ግን አንድ ነገር ነገረው። "ይሄማ የሚያስፈልግ ሕይወት ነው። ይሄ የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ የአንድ ጊዜ ድርጊት፤ የአንድ ወቅት ሥራም አይደለም። ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር ዕድል ፈንታ የለህም" አለው። ሕይወት ነው፤ እኔን የምትቀበለኝ ከእነ አገልጋይነቱ ከእነ ትህትናዬ ዝቅ ብዬ ከመምጣቴ ጋር እንጂ በትልቅነቴ ብቻ አታገኘኝም፣ የእኔም አትሆንም። ከእኔ ጋር ኅብረት የሚኖርህ ትልቅነቴንም፣ አግር ማጠቤንም ጨምረህ ስትቀበለው ነው። እነዚህ ሁለቱ የሚነጣጠሉ አይደሉም። ለእኔ አገልጋይነት ከፍታም፣ ዝቅታም ነው ብሎ ዘጋበት።

በአገልጋይነት ሕይወት ውስጥ ከፍታም ሆነ ዝቅታ ሁለቱ የሚነጣጠሉ አይደሉም። አማዚአብሔር የቱንም ያህል ቢያከብረን፣ ቢሞላልን፣ ቢሳካልን፣ ቢሆንልን፣ ቢሰምርልን፣ በሰዎች እፍ ገበተን ተነግሮልን የማያልቅ ሰዎች ብንሆንም፣ የቱንም ያህል ቢቆልሉን ክፍታን ከዝቅታ ከነጣጠልነው ዋጋ የለውም። አስተውሉ ያኛው ከፍታዬ ከሰዎች ሲለየኝ፣ ይሄኛው ዝቅታ ግን ከጌታ ጋር ኅብረት እንዲኖረኝ ነው የሚያደርገኝ። እናም ከጌታ ጋር ህብረት የሚኖረኝ በዚህ ነው። ዝቅ ብዬ አግርህን ልጠብ የሚለውን ካለተቀበልከው ከእኔ ጋር ህብረት የለህም ነው የሚለን ጌታ። እናንት ወንኖቼ ሆይ! እርሱ የአማዚአብሔር ልጅ ከሰዎች ልጅ ጋር ኅብረት ለማድረግ ይህንን ማድረግ ካስፈለገው፤ እኛስ ዝቅ ብለን እርስ በርሳችን ምን ያህል ኅብረት ማድረግ ያስፈልገን

ይሆን?

አለቲ እግር ሊያጥብ ወደ ጀመረበት ቦታ ወደ ቁጥር አሰራ ሰባት አንደኛ ልመልሳችሁ። አንደኛ ተላልፎ የሚሰጥበት ሰዓቱ ደርሷል። በጣም እጭር ጊዜ ነው ያለው። የአርሱም ልብ ከብዷል። ልሞት ነው አያላቸው ነው። በዚያ ስለ ሞት በሚታሰብበት መካከል "አግራችሁን ልጠባችሁ" ብሎ ሲነሳ የሰሙት ሰዎች አልተረዱትም፤ ሐሳቡን የደገፈውም ሰው አልነበረም። ይሆን ነገሩንም አልወደዱለትም። የሚመች ባይሆንም ላገልግል ብሎ ግን ተነሳ። ማገልገሉንም ጀመረ። ኢያችሁ አገልጋይነት ህይወት የሚሆነው አዚህ ላይ ነው። ሲመቸንም ሳይመቸንም፣ ሰዎች ሲረዱልንም ሆነ ሳይረዱልን እግዚአብሔር እንድናገለግለው ይፈልጋል። ጌታ ተነስቶ እግር ማጠቡን ቀጠለ። ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስን መምሰል የምንችልበት መንገድ ጌታ አርሱ ያደረገውን ነገር በማድረግ ነው።

በአገልጋይነት ሕይወታችን እግዚአብሔር የሚከብርበት እና የሚጠቀምበት ሰው የምንሆነው፤ ያገኘናቸውን ማናቸውንም አድሎች ተጠቅመን ስናገለግልበት ብቻ ነው። ታዲያ አገልጋይ ለመሆን ምን አናድርግ? አንደኛ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አገልግሎት ፈጻሚዎች መሆናችንን ትተን አገልጋይ ለመሆን የአገልጋይነት የሕይወት ሥርዓትን መከተል ይኖርብናል። አገልጋይ ለመሆን ሕይወታችን፣ መንገዳችን፣ አቅጣጫችን፣ አስተሳለባችን መቀየር አለበት። የብዙ ለዎች ትኩረታቸው በሚሰሩት ሥራ ላይ እና ለርቼዋለሁ በሚለው ስሜት በመሟሟቃቸው ላይ ነው። እግዚአብሔር ግን የሚፈልገው ሰርተን ስንጨርስ "የማልጠቅም ባርያ ነኝ" በል ነው የሚለው። እያችሁ ባርያ መሆናችንን ነው የሚናገረው። ሁለተኛ የምናደርገው ለሌላው ሰው የጎደለበትን ለመሙላት፣ ችርነት፣ ምህረት፣ በጎነት ለማድረግ ነው። ባልጌደራ ፈላጊዎች ከምንሆን ባልጌደራ ለመሆን ብንሮጥ ይሻላል።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14÷21 ላይ ጌታ ግብዣ ባደረከ ጊዜ ብድራት ሊመልሱልህ የሚችሉትን ሰዎች አትጥራ። ይልቅስ *"ቶሎ ብለህ ወደ ከተማው አውራ ጎዳናዎችና መተላለፊያ መንገዶች ውጣ፤ ድሆችንና አክለ ሰንክሉሎችን ዓይነ ስውሮችንና ለንካሶችን ወደዚህ አሰገባቸው"* ብድራትህን በትንሣኤው ታገኘዋለህ ብሎ ይናገራል። የማናየውን እግዚአብሔርን በምናያቸው ሰዎች ውስጥ ሰርፀን መውደድ እና ማገልገል። ይሄ እንዴት ያለ መባረክ ነው! አርሱ የሰጠንን በረከት መልሰን ልንሰጠው የማንችለውን

ልናደርግ የምንችለው በአምሳሉ ወደ ፈጠራቸው ለዎች መድረስ ብቻ ነው።

እንዳንድ ጊዜ ሰንጸልይ፣ ቃሉን ሰናነብ፣ "ተገለጥልኝ" ሰንለው፣ የማናውቀውን ሁሉ ግልጥልጥ አድርጎ ጌታ ቢናገረን፣ ሁሉን ፍትትትት አድርጎ ቢያሰተምረን ይህንን ሁሉ ምስጢር ተቀብዬ ምንድነው የማደርግበት? ብዬ አስባለሁ። እግዚአብሔር የማደርግበትን ነገር እስክ ማውቅ ድረስ የሚጠብቅ ይመስለኛል። አግዚአብሔር ልቤ መስተካከሉን፣ አዕምሮዬ ማስተዋል፣ ውስጤ ጥበብ ማግኘቱን የሚጠብቅ ይመሰለኛል። የጠየከኝን አብዝቼ ሳልሰፍር ነው የምሰጥህ፤ ጸጋውን ግን ብሰጥህ ምን ታደርግበታለህ? ይለኛል። ምክንያቱም ስጦታውን የማባክን፣ የማዝረከርክ ከሆነ እንዳባክነውና እንድጠፋበት አይፈልግምና።

አግዚአብሔር አብልጦ ይባርካችሁ፣ ይስጣችሁ፣ ይሙላላችሁ፣ አንዳች ነገር ሳታጡ አትርፋችሁ የምትኖሩ ህዝብ ያድርጋችሁ። የአግዚአብሔር ኪዳን አርሱ ነው፤ ያደርጋችኋል። ግን ደግሞ እግዚአብሔር ይሄንን ጥያቄ አብሮ ይጠይቃል። "ብለጥህ ምን ትሰራቢታለህ?" ተቀብዬ ምንድነው የማደርግበት? አነዚህ አሁን በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የፖለቲካ ችግር ገጥሟቸው ከስልጣናቸው የሚወገዱ መሪዎች ከአገራቸው ህዝብ በዘረፋ የሰበሰቡት በሚሊዮኖች እና በቢሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር የባንክ ሒሳባቸው ውስጥ ታገደባቸው ሲባሉና ስሰማ ይሆን ያህል መጠን ያለው ገንዘብ ያከማቹት ምን ሊሰሩበት ነበር? ብዬ አስባለሁ። ወይም ደግሞ ሰው ሲሞት ጥሎት የሚሄደውን ነገር ስታሰቡ፤ አወይ ሰው ዕድሜ ዘመኑን የደከመለትን ስንቱን ነገር ትቶት ሄደ፤ ትላላችሁ። እንግዲህ ምንም ሳይሰሩበትና ሳያተርፉበት ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ጥቅም ላያውሉት ቀረ ማለታችሁ ነው።

ሦስተኛው አገልግሎት አኛ የምንፈጥረው ነው። በዚህ ላገልግል ብለን ራሳቸንን አኛው በወሰንነው አና በመረጥነው መስክ እያሰማራን በፍቅር የምናገለግለውን አገልግሎት እንፍጠር። አገልግሎት የለዎችን ችግር በመቅረፍ ለእግዚአብሔር ክብር ለሰዎች ደግሞ ምስጋናን ለጌታ እንዲያሰገኝ የምንሰራው ሥራ ነው። ጉድለቱ አዚሁ በመካከላችን ወይም በውጪ ያለ ሊሆን ይችላል። ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበትን ነገር ልናደርግ ይገባናል።

በዚህ ጉዳይ አንድ ለው ተከራክሮኛል። አንድ ጊዜ ከሥራ ወጥቼ ወደ ቤት ስሄድ ሁሉቱም የመኪናዬ ጎማ ስለተነፈሰብኝ ቆመኩ። የዚያን ዕለት ጸሐዩዋ በጣም

ታቃጥል፤ አየሩም ሞቃታማ ነበር። በዚያ ላይ ባርኔጣዬን እንኳ አላደረኩም ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ገብቶኝ ቆሜ እያለሁ፤ አንድ ሰው አይቶኝ መኪናውን አዙሮ ወደ እኔ መጣ። አጠገቤ እንደ ደረሰም "ምን ችግር ገጥሞህ ነው የቆምከው?" አለኝ። ሁለቱም ጎማ ተኝቶብኝ ነው አልኩት። ምን አለፋችሁ ተፍ ተፍ ብሎ ጎማውን አየቀየረልኝ፤ እኔም የአቅሜን አየረዳሁት ማውራት ጀመርን። ከዚያም ለለ ጌታ ስለሚረው በጌታ እንደሆነ ነገረኝ። ይህን ስለማ ደስ አለኝ። እናም በደንብ አርጎ አስተካክሎ መጨረሻ ላይ ጎማዬን ጭኖልኝ ሊሄድ ሲል "ሰምን ይሄንን ቸርነት አደረከልኝ?" ስል ጠየቅሁት። "አይ ወንድሜ ሆይ ይሄ ለእኔ አገልግሎቴ ነው" አለኝ። እንዲህ ያለውን አገልግሎት ለምቼው የማላወቀው ነገር ስለሆነብኝ "የየትኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ነህ? አገልግሎትህስ ምንድነው?" ስል ጠየቅኩት። እርሱም "በታ እኔ ለዎች መንገድ ላይ የመኪና መበላሸት ችግር ሲገጥማቸው ለመርዳት ለጌታ ቃል ገብቻለሁ። ይህን አገልግሎት ለመስጠት መኪናዬ ሁሌም ዝግጁ ናት። ርዳታውን የምሰጥበትም መፍቻ መሳሪያዎች አሉኝ፤ ይገርው አዞራለሁ" ብሎ ነገረኝ። ይሄ ትልቅ ስብከት ውስጤ ገብቶ ቀረ። በመጨረሻም አድራሻውንም ሳይሰጠኝ ተቻኩሎ ትቶኝ ሄደ። አያችሁ አገልግሎት የሚፈጠር ነገር ነው። አገልጋይ ለሆነ ለው አገልግሎት የሚፈጠር እና በሚሄድበት ስፍራ ሁሉ የሚያገኘው ደግሞም የሚፈጽመው ነገር ነው።

በመጨረሻም ስናገለግል ደስ እያለን እናገልግል። ለምን? ትዝ ይላችሁ እንደሆነ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እንደ ወደዳቸው ነው ቃሉ የሚናገረው። ጌታ አገልጋይነቱን በፍቅር እየወደደው ይፈጽም ስለነበር የተማሪዎቹን እግር በማጠቡ ምንም አልከፋውም። አገልግሎትን የሚያቀጣጥለው ነዳጅ ፍቅር ለለሆነ ጌታ እግራቸውን ያጠባቸው እየወደዳቸው ነበር።

እንዳንድ ጊዜ አገልግለን ምሰጋና ፈልገን እናጣና እንናደዳለን፤ ተሰፋም እንቆርጣለን። ሁለተኛም አጠገባቸው አልደርስ እንልና ፍቅሩ ግድ ሲለን ደግሞ ተመልሰን እንሄዳለን።

እናቶች ልጆቻቸውን ምን ያህል እንደሚያገለግሏቸው ተመልከቱ። "እንዲያ እንዲያደርጉ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው?" ስንል ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ነው።

ባለ ትዳሮች እንዲሸካከሙ፣ እንዲቀባበሉ የሚያደርጋቸው ነገር ፍቅራቸው ነው። ወገኖቼ ሆይ! ፍቅሩ ባለበት ቦታ ላይ ለረጅም ጊዜ በደስታ ማገልገል ይቻላልና

ደስ እያላችሁ አገልግሉ። ደስ እያለን የምናገለግልበት ሁለተኛው ምክንያት የምናገለግለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሆነ ነው። በቆላስይስ መልዕክት ምዕራፍ 3፡13 ላይ *"በእርሱ በክፉ ለሉ ማዚአብሔር አብ ምስጋና አያቀረባችሁ በቃልም ሆነ በተግባር ያደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ሰም አድርጉት"* ይለናል። ሐዋርያው ይህን አድርጉ የሚላቸው ለሠራተኞቹ ነው። የምታገለግሉት ሰው አመጸኛ፣ ከፋ አለቃ ወይም መስሪ ሊሆን ይችላል። ብድራት አላችሁና፣ የምትሰሩትም ለጌታ ነውና ሥራችሁን እየወደዳችሁት ጌታ እንደሚያያችሁና ደስ እንደሚሰኝበትም እያሰባችሁ ሥሩ።

ወገኖቼ ሆይ! ደመወዙችን ምድራዊ ቢሆን ኖሮ እንዴት ምስኪኖች በሆንን ነበር። እውን ግን ዋጋችን ከምድር ሳይሆን ከሰማይ ነው። ብድራታችን ያለው ሁሉን ከሚችል ጌታ ክአማዚአብሔር ዘንድ ስለሆነ፤ ብድራታችንን ከሰው እንጠብቅም። እርሱ ሂሳብ አያሳስትም። በእርሱ ዘንድ እመጻ የለም። እያንዳንዱ ሰው ሥራው፣ ድካሙና አገልግሎቱ ተመዝግቦ በመጽሐፍ አለ። ልብን የሚመረምር እግዚአብሔር እምላክ ፈትሾ እያንዳንዱን እንደ ሥራው ይከፍለዋል። ስለዚህ ተስፋ አትቁረጡ። የምታገለግሉት ጌታን ስለሆነ ስታገለግሉ ደስ እያላችሁ አገልግሉ። ጌታ ሰለ አገልጋይነት የተወልንን ምሳሌ ለሁለት ነገር ልጠቀምበት እችላለሁ። አንደኛው እግዚአብሔርን ለማክበር ሁለተኛው ደግሞ ለሰዎች ጥቅም እንዲሆን። ይሄ በሁላችንም እጅ ያለ ነው። ማንኛውም የወንጌል አማኝ የአግር ማጠቢያ ሳህን፣ ውሃ እና ማበሻ ፎጣ የሌለው የለም። በመካከላችን አግዚአብሔርንም ሆነ ለዎችን የሚያገለግልበት ነገር የሌለው ሰው ይኖራል ተብሎም አይታሰብም።

አያችሁ! አገልግሎት የምርጫ ጉዳይ ነው። ዕድሉ አለ። እኔ ግን ማገልገል ሥርጫዬ ነው ወይ? ነው ጥያቄው። አገልግሎት ምርጫ ነው፣ ዕድልም ነው። እስኪ ጊዮችን ኢየሱስን እና ጲላጦስን ጎን ለጎን እድርገን እናነጻጽራቸው።

ጌታ የመጨረሻውን ራት በበላባት ምሽት እና አልፎ ከተሰጠ በኋላ በነበረው ግማስት ለኢየሱስም ሆነ ለጲላጦስ ተመሳሳይ ዕድል ቀርቦላቸው ነበር። በመታጠቢያ ሳህን የተሞላ ውሃ እና ማበሻ ጨርቅ። ሁለቱም በቀረበላቸው ዕድል ላይ የየራሳቸውን የሥርጫ ዕጣ ጥለዋል። ጌታችን ኢየሱስ ማበሻ ጨርቁን ወስዶ በሳህኑ ውሃ ሞልቶ ዝቅ ብሎ በጣም ወርዶ የይሁዳን እግር ሳይቀር የደቀ መዛሙርቱን እግር እጠበ፣ በጨርቁም አበሰላቸው። እግሩን ላለመታጠብ ያንገራገረውን እግሩን የማያጥበው ከሆነ ግን ከእርሱ

ጋር ምንም ዕድል ፈንታ እንደሌለው ቁርጡን የነገረውን ጴጥሮስን ጭምር። በዚያች የምጥ እና የጭንቀት ወቅት ሰዓቲቱ እንደ ደረሰች እያወቀ ሌሎችን ሊያገለግል ወደደ።

ጲላጦስስ? በማግስቱ ምን ነበር ያደረገው? እርሱም የቀረበለትን ዕድል በራሱ መንገድ ተጠቅሞበታል። በማጠቢያ ሳህኑ ውስጥ ባለው ውሃ በመታጠብ ኢየሱስን ይፈታው ዘንድ እየቻለ እና ለመፍታትም በቂ ምክንያት እያለው ራሱን ከተጣያቂነት ለማስመለጥ ተጠቅሞበታል።

"እኔ ከዚህ ሰው ደም ንፁህ ነኝ" በማለት በተቀመጠበት የፍርድ ዙፋን ላይ እጁን በመታጠብ የወደደውን አድርጓል። እያችሁ! ለዚህ ነው እገልግሎት ምርጫ ነው ያልነው። ጌታ ዕድሉን ተጠቅሞበት ውሃውን እና ማበሻውን በቤት ውስጥ ሲያገለግልበት· ጲላጦስ በፍርድ አደባባይ ላይ ለራሱ ስም እና ክብር ማስጠበቂያነት ተጠቅሞበታል።

እግዚአብሔር እንዴት እንደባረካችሁ እጃችሁን፣ ቤታችሁን፣ አዕምሯችሁን፣ ልባችሁን እዩት። እግዚአብሔር በአናንተ ውስጥ ያላፈሰሰው ጸጋ ምንድነው? እግዚአብሔር ያልከፈተላችሁ የሰማይ ደጅ ምን አለ? እግዚአብሔር በምክሩ ገልጦላችሁ የሰማይን ምስጢር አውቃችኋል። አሁን ምርጫው የእኛ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሁሌ የሚጠይቀው ጥያቄ ያንን ነው። "ሕይወትህን ምን ሰራህበት?" ነው የሚለው። "የሰጠሁህን መልካም ዕድሎች ምን አደረግካቸው?" እኔም ራሴን ሁልጊዜ የምጠይቀው ነገር "የሰጠኝን ሊደራ ምን አደረኩበት?" ብዬ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል የምንችልበት አንዱ መንገድ እገልጋይ በመሆን ነው።

ምዕራፍ 6

ራሳችሁን ለመሥዋዕትነት አዘጋጁ!

ምዕራፍ ስድስት

ራሳችሁን ለመሥዋዕትነት አዘጋጁ!

በዚህ ምዕራፍ ላይ የምንመለከተው እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ ስለ መሥዋዕትነት ይሆናል። ይሄ ደግሞ ለሁላችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። መሥዋዕትነትን በሚመለከት ብዙጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር የሚሰማ አንድ ምሳሌ አለ።

በአንድ ባለጠጋ ገበሬ ቤት ውስጥ አብረው ይኖሩ የነበሩ አንድ አሳማ እና አንዲት ዶሮ ነበሩ። አሳማው እና ዶሮዋ እንድ ቀን ግቢው ውስጥ እየተጫወቱ ሳለ ዶሮዋ ለአሳማው "ጌታችንን ደስ ለማሰኘት አንዳንድ ነገር ብናዋጣ ምን ይመስልሃል?" ስትል ጥያቄዋን አቀረበችለት። አሳማውም ሲመልስላት "ሴትዮ አርፈሽ ተቀመጪ! አንቺ እኮ ላዋጣ ብትይ የምታዋጪው መዋጮ አንቁላልሽን ብቻ ነው፤ እኔ የሚጠበቅብኝ ግን መሥዋዕትነት ነው" አላት ይባላል።

እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ የሚፈልገው መዋጮ መሥዋዕትነት ነው። ይህንን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት መመልከት እንችላለን። ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ሰማጠብ በተነሳ ጊዜ የያዙቸው ማበሻ ጨርቁ እና የውሃ መያዣው እቃ አገልጋይነቱን እንደሚያስታውሱን ሁሉ፤ መሰቀሉ ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስን መሥዋዕትነት ያስታውሰናል።

ይህ መሥዋዕትነት ግን በመጨረሻው ሰዓት ላይ የተሰቀለበትን እና ነፍሱን አሳልፎ የሰጠበትን ቦታ ብቻ ሳይሆን፤ መሰቀሉን ጨምሮ በአጠቃላይ የኖረውን መላ የመሥዋዕትነት ሕይወቱንም ነው የሚያመለክተን። ዋጋ እየከፈለ በመሥዋዕትነት የኖረውን ኑሮ ሁሉ፤ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያለውን የሚያስታውሰን ሊሆን ይገባል።

ይህ የመሰቀሉ ነገር በከርሰትና ሕይወታችን ለእረፍት የተጠራንበትና በእግዚአብሔር ደስታና ሰላም የምንመላለስበት ቢሆንም እንኳ፤ ይህን ሕይወት የሰጠን ከርሰቶስ ኢየሱስ ራሱ ይህን ትልቅ ደስታ ያገኘው በመሥዋዕትነት ሕይወት ውስጥ እልፎ በመሄድ ስለሆነ፤ በውስጡ ምንም ዓይነት የመሰቀል፣ ዋጋ የመክፈል፣ እና የሕይወት መሥዋዕትነት የለበትም ብንል እንዋሻለን።

ጳውሎስ ለፈልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ ምዕራፍ 3÷10-11 ላይ *"ጌርሱንና የትንሣኤውን ኃይል ለንዳውቅ በመከራው ለንድካፈል ወደ ሙታን ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በማቱ ለንድመሰለው ለመኛለሁ"* ብሎ ይናገራል። ይሄ ምን ዓይነት ምኞት ነው? እንዲያው እንዲህ ዓይነቱን ምኞት በዚህ ዘመን በእኛ መካከል ያለ ሰው ቢሰማው "ምነው ወንድሜ ደህና ነገር አትመኝም እንዴ?" ነበር የሚለው። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለተጻፈ እኛም በእከብሮት ሰለምንይዘው ነው እንጂ፤ ሰው ይሄ ቢሆንልኝ በኢየሱስ ሞት መካፈል አፈልጋለሁ። በመከራው ጎብረት ማድረግ አፈልጋለሁ፤ በመሥዋዕቱ ማለፍ አፈልጋለሁ፤ የሚለው ነገር ከባድ ሐሳብ እንደሆነ እናውቃለን። ቢያስፈራም፤ አስደናቂ የሆነ ምኞት ነው።

መሥዋዕትነቱ የሌሎች ነገሮች ሁሉ ቁንጮ ስለሆነ ያስፈልገናል። ቀደም ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ወደ እግዚአብሔር ስለ መጢጋት፣ ስለ አገልጋይነት፣ ኑሮን ስለ ማቅለል፣ ዮቢዎና የፀጥታ ጊዜ ስለ መውሰድ ተነጋግረናል። ከእነዚህ ሌላም በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ ሌሎችም የምናነሳቸው ልዩ ልዩ ልምምዶች በሙሉ ቢደመሩ፤ አሁን እንደምንነጋገርበት የመሥዋዕትነት ሕይወት አይሆኑም።

የመሥዋዕትነት ሕይወትን መኖር ጥበቅ የሕይወት ምሳሌነትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በጥልቀት እናየዋለን። ይህ ሐሳብ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። እንዲያውም አሁን አሁን የመጡ ይህን የሚገዳደሩ ብዙ እንግዳ ትምህርቶች አሉ።

መቼስ በዚህ ባለንበት ዘመን የመንፈሳዊ መጽሐፉ፣ የስብከቱ፣ እና የትምህርቱ እበዛዝ ጉድ የሚያሰኝ ነው። መብዛቱ ባልከፋ ነበር። ችግሩ ያለው ግን ለአድማጩ ወይም ለተደራሲው ሕዝብ የሚያስተላልፈው ፍሬ ሐሳብ ላይ ነው። መፈተሽ ያለበትም ተደራሲው ወይም አድማጩ ሕዝብ ዘንድ ሲደርሱ የሚያስገኙት ውጤት ነው።

በዚህ ከፍል ካነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መልኩ፤ በዚህ ዘመን ያለ

ሃንም ውጣ ውረድ ዋጋ ሳይከፈልበት፣ መሥዋዕትነት ሳይኖርበት፣ እንዲሁ በዋል ፈሰስ የሆነ ሕይወት እየተኖረ በስኬት የተሞላ የክርስትና ሕይወት እንደሚኖር የሚያስተምሩ ሠስቀል አልባ ግና ክርስትና አስተኔ (ክርስትና መሰል) ትምህርቶች መኖራቸውን እናውቃለን።

በክርስትና ውስጥ መሥዋዕትነት መከፈል አሊያም ስለ ክርስቲያናዊ መሥዋዕትነት መስበክም ሆነ ማስተማር እምነት የለሽ ወይም ተሸናፊ ያሰኝ ስለመሆኑ የሚሰብኩ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱን ክርስትና ከየት አቅጣጫ እንደ ተረዱት ለማወቅ ያቸግራል። መሥዋዕትነት ያለበት ክርስቲያናዊ ሕይወት ግን የለንቋሳ ሳይሆን፤ የብርቱ ክርስቲያን መለያው ነው። ያለ መሥዋዕትነት ሕይወት እንዲሁ በእምነት ብቻ በእግዚአብሔር ፊት የመከበር፣ ምገሱን የመላበስ ነገር በወርቅ ሰሃን ላይ ሆጨጭ እንዳለ አነቁ ተዘርግፎ አይቀርብልንም። የክርስትና ትምህርትም ሆነ ሕይወት ቆምጨጭ፣ መረር ከሚልባቸው ምክንያቶች እንዱ መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ የመሆኑ ጉዳይ ነው።

አንዱ ወንድማችን ሲያስተምር እግዚአብሔር ሲልከን አስቀድመን "ለእኔ ይመቸኛል ወይ?" ብለን ነው የምንጠይቀው ብሏል። ይህ ቃል በጣም ነው ልቤ ውስጥ የቀረው። እግዚአብሔር እናደርግ የሚገባንን ሥራ እንሠራ ዘንድ ለትውልዳችን መልዕክተኞች እድርጎ ሲልከን፣ እና በባለ አደራነት ሲያስቀምጠን "ለእኔ የሚመች ነው ወይ?" ብለን መጠየቃችን አሳዛኝ ነው። ክርስቲያናዊ የመሥዋዕትነት ሕይወት ግን ይሄንን አይፈቅድም። ለመሆኑ ይህ ዓይነቱ የመሥዋዕትነት ሕይወት ምን ዓይነት ሕይወት ነው? መሥዋዕትነት ስንልስ ምን ማለታችን ነው?

መሥዋዕትነት የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ዘመን በጣም የታወቀ ሐሳብ ሲሆን፤ ከዘጸዓት ጀምሮ በዘሌዋውያን፣ በዘኁልቁ እና በዘዳግም መጻሕፍት ሁሉ ውስጥ የምናገኘው፤ ከዚያም ባለፈ በነቢያቱም መጻሕፍት ውስጥ የተገለጸ ነው። "መሥዋዕትነት" ወይም "መባ" የሚለው ሐሳብ፤ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር በሚቀርብበት ጊዜ ይዞት የሚቀርበውና በመታረድ የሚሞት ወይም ደግሞ ፈጽሞ በእሳት የሚቃጠል መሥዋዕት ነው።

ለዎች በሙሴ ሕግ የተፈቀደውን አንድን የእንስሳ መሥዋዕት ይዘው ሲቀርቡ፤ መሥዋዕቱ መቃጠል ወይም መታረድ እንዳለበት ሁሉ፤ እኛም ከዚህ አጠቃላይ ሐሳብ በመነሳት፤ ለመሥዋዕትነት ስንጠራ ለፈቃዳችን መሞት፣ የራሳችንን ምኞት እና

ፍላጎቶችን መማደል ይጠበቅብናል ማለት ነው። ለፈቃዳችን ስንሞት፣ እና የራሳችንን ምኞት እና ፍላጎቶች ለንደል ምንድነው የምንሆነው? የሚለውን የአዲስ ኪዳኑን ትከከለኛ ሐሳብ ማግኘት ወይም መረዳት በጣም ያስፈልገናል። መሥዋዕትነት በብሉይ ኪዳን ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ማሚላት ነበረበት።

የመጀመሪያው እግዚአብሔር ደስ የሚለኝበት፣ በእግዚአብሔር የተወደደ፣ ሁለተኛው ንጹህ ወይም ነውር የሌለበት፣ ሦስተኛው ደግሞ መሞት ወይ መቃጠል የሚኖርበት ነው። ታዲያ እነዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያላቸው አስተሳሰብ ምንድነው?

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ 12፥1-2 ላይ *"እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁ ለማዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ ለምናችኋለሁ፣ አርሱም ለእለምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ አርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ"* ብሎናል።

ሐዋርያው እነዚህን የሮሜን እማኞችን መለመን ለምን አስፈለገው? የለመናቸው፤ ሰው ለውነቱን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እና ሕያው፣ ቅዱስም መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን በቀላሉ እሺ ብሎ የሚቀበለው ነገር ስላይደለ ነው። ለሥጋ፣ ለእለምሮ የሚመች ነገር ስላይደለ እና በውስጡ ዋጋ የሚጠይቅ የሚኮስኩስ ነገር ስላለው ነው። እንዲያቀርቡ የጠየቃቸው ሰውነታቸውን እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን የበጎችን ወይም የሌላ እንስሳን መሥዋዕት አይደለም። ለውነታቸውን፣ ሥጋቸውን፣ ማንነታቸውን፣ እናንተነታቸውን ለእግዚአብሔር አቅርቡ ነው የሚላቸው።

በቀደመው ኪዳን ውስጥ እስራኤላውያኑ ይዘው የሚቀርቡት እንስሳ ስለሆነ ምንም ችግር አልነበረውም። እንስሳውን ጎትተው ያመጡታል፤ ለመሳተት ካሰቸገራቸው ደግሞ በተለይ ከሩቅ አገር የሚመጡ ከሆነ፣ እንስሶቸውን እዚያው በሚኖሩበት አገር ይሸጡትና ገንዘቡን ይዘው በመምጣት እዚያው ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከሻሮጮች እና ለዋጮች ላይ ገዝተው ይዘው ይቀርቡ ነበር። ብቻ እንስሳው ንጹህ እና ነውር ወይም ነቀፋ የሌለበት በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ይሁን እንጂ።

በአዲሱ ኪዳን ግን ራሳችሁን አቅርቡ ስለሚል፤ የሚጎተት፣ የሚሸጥ፣ የሚለወጥ እንስሳ የለም፣ ስለዚህ ጳውሎስ "እለምናችኋለሁ" የሚለው ራሳቸውን ሕያው

መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ ነው። ሕያው መሥዋዕት እንዴት ይኮናል? ከላይ እንደ ተናገርኩት መሥዋዕቱ በአግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሚኖረው በመታረድ ወይም በመቃጠል ሲሞት ነው። እዚህ ላይ ጳውሎስ "ራሳችሁን ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ" የሚለው ሐሳብ ራሱ ግር የሚል፣ እርሰ በርሱም የሚጋጭ ነገር ይመስላል። መሥዋዕት ከሆነ መሞት አለበት። ግን ደግሞ ሕያው የሆነ አድርጋችሁ አቅርቡ ነው የሚለን። ይሄንን መፍታት በጣም ያስፈልገናል። መሞት አያለበት ግን ደግሞ እንዴት ሕያው ሊሆን ይችላል? ራሳችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን የምናቀርበውስ እንዴት ነው? ይሄንን የአዲስ ኪዳን አስተሳሰብ ከተረዳን እንዴት በመሥዋዕትነት መኖር እንዳለብን መጨበጥ እንችላለን።

ጳውሎስ በሮሜ 15÷15-16 ላይ *"እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ መሠረት አንደገና ለሳስባችሁ ዘንድ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በድፍረት የጻፍሁላችሁ፤ በእግዚአብሔር ወንጌል የክህነት ተግባር፣ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ ለመሆን ነው፤ ይሽውም አህዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ለንዲሆኑ ነው* ይለናል።

ሐዋርያው እዚህ ላይ እየተናገረ ያለው አህዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የተወደደ መሥዋዕት እንዲሆኑ፤ እኔ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልኩ ነው የሚለው። እኔ የማገለግለው፣ እኔ የምሮጠው፤ አሕዛብ እንደዚህ ለእግዚአብሔር የተወደደ መሥዋዕት እንዲሆኑ፣ እንዲሞቱ ሳይሆን፤ ሕያው መሥዋዕት ሆነው በጌታ ፊት እንዲቀርቡ ነው። ይሄ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ዳላስ ዊላል የተባለ ሰው የመሥዋዕትነትን ምንነት እና ትርጉም በተመለከተ በጻፈው መጽሐፉ ሲገልጸው፤ "መሥዋዕትነት ማለት ለእኛ የሆነው እና የሚያስፈልገንን ነገር ለሌላው ሰው ጥቅም ብለን መልቀቅ፣ መተው ማለት ነው" ይለዋል። ይሄ መልቀቅ፣ መተው ወይም መካድ የሚለው ሐሳብ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እጅግ ዋና የሆነ ነገር ነው። ጳውሎስ "በዚህች ዓለም የሚጠቀሙ እንደማይጠቀሙ ይሁኑ" እንደሚለው ምስጢር ማለት ነው።

ወይዘሮ ሜሪ የምትባል አንዲት ባለ ትዳር እና የሁለት ልጆች እናት ነበረች። ሜሪ አብሮ አደግ ጓደኞቿ ሲያገቧት የሚጠይቋት ልቧን የሚያርደው እና የምትሸሸው አንድ ጥያቄ አለ። ይህ ጥያቄም "ምን እየሠራሽ ነው ያለሽው?" የሚለው ነው። "እኔ

የቤት እመቤት ነኝ። ቤት ውስጥ ሁለት ልጆቼን አሳድጋለሁ" ስትላቸው ከዚያ በኋላ ያለውን የሚያዳምጣት ሰው አይኖርም። ይሄ ነው ብላ የምታወራው ሌላ ትልቅ ነገር ስለሌላት ማለት ነው። የቤት እመቤትነት ብዙ የሚደመጥ ተግባር አይደለም ለእነርሱ፤ ሁለት ልጆች ማሳደግስ አዲስ ነገር አይደል!

እናም ሜሪ በየቢዜው ይሄን ጥያቄ መጠየቋ በጣም ስለሰለቻት እንድን አቀርቅራ "እኔ የልጆች እናት ነኝ፤ ቤት ውስጥ ነው የምውለው" ማለቱን እትወደውም፤ ለነገሩ በቤት ውስጥ የቤት እመቤት መሆንን በምርጫዋ የወለነችው ነገር ነው። እናም አንድ ቀን አለበቸና አንድ ዘዴ ፈጠረች። ዘዴው ምንድነው፤ ማንም ለው የትም ቦታ ምንድነው የምትሠሪው? ብሎ ከጠየቃት መልሷ "የልጆች ሰፔሻሊስት ነኝ፤ ሥራዬም በልጆች እና በወላጆች መካከል መልካም ግንኙት አንዲኖር ማድረግ፣ አባት በቢዜ ወደ ቤቱ መግባትን አንዲያስብና በትዳሩ ውስጥ በሚጠበቅበት ድርሻውም ተገቢ ሚናውን እንዲጫወት የሚያደርግ ምክር መስጠት ነው" ልትል። "ሰፔሻሊስት" ናትና ይሆን ስትላቸው በደንብ ያዳምጧት ጀመር።

ሜሪን ወደዚህ ሐሳብ አንድትመጣ ያደረጋት ነገር ምንድነው? ልጆቿን በአግዚአብሔር መንገድ ማሳደጓ፣ ትዳሯን በትከከለኛው መንገድ ለመያዝ ራሷን መለጠቷ፣ ከባሏ ጋር አብራ በመኖር ይሄን ትልቁን ሕይወት ለመገንባት የምትኖረውን የመሥዋዕትነትን ሕይወት አንዲሁ "የቤት እመቤት እና የልጆች አሳዳጊ ነኝ" ብሎ ማለቁ ራሷን ስላሳነሰባት ነበር። ይህን ሐሳብ በሁላችንም ዘንድ እንደገና እንድናየው አፈልጋለሁ። ሕይወታችንን በመሥዋዕትነት እንድንኖረው ያሻናል። አግዚአብሔር የሰጠን ያ መሥዋዕትነት ምን እንደሆነ ተረድተን ከጌታ ኢየሱስ ሕይወት ተመልከተን እኛ አርሱን ልንመስል፣ እርሱ በተጓዘበት የመስቀል መንገድ ብንጓዝ ያ በእርግጥ የአግዚአብሔር ወዳጆች ያደርገናል።

ጌታ ኢየሱስ ከርስቶስ በዮሐንስ 12፥24 ላይ *"እውነት እውነት እላቸኋለሁ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች። ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች"* ይላል። የጌታ ሕይወት ምስጢሩ የመሥዋዕትነት ኑሮ መኖሩ ነው። ስንዴዋ መሬት ወድቃ አፈር በለበሰች፣ አፈሩን እየጣሰች ወደ ውስጥ በገባች ቁጥር ወደ ላይ የመውጣቷ አድል ሰፊ ነው። አየሞተች ስትበሰብስ ብዙ ሆና ሽቅብ ማደጓ አይቀርም። የጌታ ሕይወት ምስጢሩ ይህ ነው። ነገሩ ያለው ፈውስ፣ ተዓምራት ሚድረጉ ላይ

ሳይሆን፤ እርሱ የመሥዋዕትነት ሕይወት ለመኖር መፍቀዱ እና በዚያ መትጋቱ ላይ ነው።

በአርሻ ማሳ አጠገብ ስታልፉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? የበቆሎ አርሻ አዝመራን ተመልከቱ። ሜዳው አንዲያ በአረንጓዴ ንጣፍ መሳይ ተክል አምሮ ከላይ ወሮች በመንቆራቸው የአሸቱን ራስ አየቸረቸፉ የሚበሉት፣ ጦጣ እና ዝንጀሮዎች በየዛፉ ተንጠላጥለው ጠባቂው አስኪሰለቸው ድረስ የአሸቱን ዛሳ አየገነጠሉና ልባሱን አየሸለቀቁ ለመጋጥ ከገበሬው ጋር ግብ ግብ የሚገጥሙበት ይህ አዝመራ ኩቶውት አነሳስ ጅማሬው እንዴት ነው? በአንዱ ዘንግ የበቆሎ ተክል ላይ ሁለት ሦስት ራስ አሸት አፍርቶ ከታዘለበት አንቀልባ አፈትልኮ ቁልቁል ሾልኮ ሊወድቅ አንደ ደረሰ አንቃቅላ ህጻን ጭሬው ኩብዶት አገዳው ዘመም ብሎ ስታዩ የዚህ ተክል አነሳስ ጅማሬው አንዲሁ እንደ ዛሬው የዐይን ፈተና ሆኖ በመታየት በማስጎምጀት በማማር ነውን? ፈጽም አይደለም!

የዚህ ያማረ አሸት አመጣጥ ታሪኩ እንዲህ ነው። አጎንቁሎ አፈር ልሶ፣ አፈር ነክሶ ከወጣው ከዚህ ቡቃያ በፊት ገበሬው ማለዳ ተነስቶ ማሳው ላይ ሲበትነው፣ ሲዘራው አፈር ለብሶ በአፈር ውስጥ በስብሶ የሞተ ዘር አለ። ያ ሁሉ ዘለላ ፍሬ አንዲያ አምሮበት የቆመው፣ ያፈራው እና የጎመራው በዚያች አንዲት የዘር ቅንጣት መሥዋዕትነት በብስባሽ ሞቷ እና ትንሣኤዋ ነው። ቀዳሚው ዘር ባይሞት ኖሮ ኋለኛው አዝመራ ባልተገኘ ነበር። ዘሩ አፈር ውስጥ ባይበስብስ እና ባይሞት የአብራኩ ክፋይ የሆነው አሸት ብዙ ፍሬ ሆኖ ተንዠርግጎ ባልታየ ነበር።

ጌታ "የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች. . ." ብሎ ሲል ይህንን ማለቱ ነበር። በምድር ላይ መውደቅ መጣልም ደግሞ መሞትም መሥዋዕትነት ነው። ዘሩ ሕይወት ያለው ነገርን የሚያፈራው ከሞተ በኋላ አንደሆነ ሁሉ የጌታ ሕይወትም አንዲሁ ነው። እኛ ቀራንዮ ላይ በዕለተ አርብ የተከናወነው መሥዋዕትነት ፍሬዎች ነን። እንግዲህ እኛም ጌታን በመምሰል ባለ ብዙ ፍሬዎች አንሆን ዘንድ አንደዚህች ቅንጣት የዘር ፍሬ መሥዋዕት መሆን ይጠበቅብናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8፥9 ላይ ስለ ጌታ ኢየሱስ ሕይወት ሲናገር *"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸርነትና ስጦታውን ልግስናውን ቀምሳችኋል፤ ለውቃችኋል። ሀብታም ሲሆን በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ስለ እናንተ ደሃ ሆነ"* ይላል። እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ምንም እንደ

ሌለው ደሃ ሆኖ መጣ; ይሄ ትልቅ መሥዋዕትነት ነው። የነበረውን መለኮታዊ ከብሩን ትቶ ወደ ምድር በመምጣት የባርያን መልክ ይዞ በለው መካከል ተመላለሰ፤ እንደ ሰውም በሁሉ ነገር ተገድቦ ተገኘ። የዚያን ቀን መላዕኩቱ እንዴት ያለ መደነቅ ይሆን የተደነቁት!!

ወገኖቼ ሆይ! ሰማይ እና ምድርን በቃሉ ያጸና እርሱ፤ የእነርሱን ሕይወት በሥልጣኑ ቃል ደግፎ የያዘ እርሱ፤ በሰው እቅፍ ውስጥ ተወስኖ፣ በበረት ውስጥ ተኝቶ ሲያዩት ለዐይን ጉድ ነው!! ትልቅ፣ ትልቅ ማነስ ነው ያነሰው! ራሱን ባዶ ነው ያደረገው! እንደ ማንኛውም ሰው እየተራበ፣ እየተጠማ፣ በእግሩ በከተማ፣ በጎጠር፣ በምኩራቦች እየተዘዋወረ እንደ ሰው ተመላለሰ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ወደ እርሱ እየቀረቡ እንዲህ እና እንዲያ አድርግ፣ ዲያብሎስም "ይሄን ድንጋይ ዳቦ አድርግ" እያሉ ያለ ጊዜው በአምላካዊ ማንነቱ እንዲገለጥ ቢፈልጉ፣ ቢጎተጉቱትም፤ እርሱ ግን የባርያን መልክ በመያዝ የመሥዋዕትነት ሕይወትን ነበር የመረጠው። ስለዚህም ከፈታቸው እየተሰወረባቸው እንደ ማንኛውም ሰው መኖርን መረጠ።

በኤፌሶን ምዕራፍ 5፥1-2 ላይ *"እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ ክርስቶስ እንደ ወደደን፣ ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕትን አድርጎ እንደሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ"*።

ክርስቶስ ራሱን ስለ እኛ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ የሰጠው በመስቀሉ ላይ ሲሞት ብቻ ሳይሆን፤ በምድር ላይ በኖረው ኑሮም የመሥዋዕትነትን ሕይወት ዋጋን በመክፈልም ጭምር ነው። በዚህ ምድር የኖረው አያመቻመቸ ሳይሆን ዋጋ እየከፈለ ነው። እንድ ጊዜ በጭንቁ ሰዓት ላይ ሊይዙት ሲመጡ እጠገቡ የነበረው ጴጥሮስ ሰይፉን ከለገባው መዞ አወጣና የሰው ጆሮ ቆረጠ። ጌታ በዚህ ጊዜ ምን አለው? "ተው ይሄ አስፈልጎኝ ቢሆንማ ኖሮ አባቴን ብጠይቀው አስራ ሁለት ጭፍራ መላዕክት ሊልክልኝ ቀላል ነበር"።

ጌታ ይህንን ሲል የመሥዋዕትነት ሕይወት እየኖረ ነበር። መላዕክት በሙሉ በእንድ ጊዜ ትዕዛዝ ሊያገለግሉት ማዘዝ እየቻለ እርሱ ግን ማንም አጃቢ እንደሌለው፣ ትኩረትን እንደማይስብ ተራ ሰው ሆኖ ተመላለሰ። በፈቃዱ ያንን ሁሉ ሲተው የመሥዋዕትነት ሕይወት ኑሮን እየኖረ ነበር። ሌላ ብዙ አማራጭ እያለው፤ ቀለል ያለ ጎዳና እያለለት፣ እርሱ ግን ይህን ከባዱን መንገድ መረጠ። ምነው? ቢባል፤ መሥዋዕትነት ነዋ!

ሕይወታችን በብዙ ምርጫዎች የተከበበች ናት። ይህች ዓለም ይህን ስለምታውቅ ሁልጊዜ በምርጫዎች ከባን ዋጋ የሚያስከፍል መሥዋዕትነት ለሚጠይቀው ሳይሆን ለአለምሮም፣ ለሥጋም የሚመቸውን፣ ቀለል ባለው መንገድ ሽረር ብለን እንድንጓዝ ታባብለናለች።

ጌታ ግን "በጠባቡ በር ግቡ፤ በጠባቡ መንገድ ሂዱ" ብሎ ነው የነገረን። ሥጋችን ግን እንዲህ ያለው ነገር አይመቸውም። አካባቢያችን፣ ማህበረሰባችንም አይደግፈንም። ፈጽሞም ይህንን አይመርጥልንም። እንዲያውም የሚመቸውን መንገድ ስንመርጥ የመጀመሪያው ጥያቄ የሚነሳብን ከራሳችን ነው። እናም ራሴው ራሴን "ምን ነካህ?" ብዬ መጠየቅ እጀምራለሁ።

ከዚያም አጠገቤ ያለው ለው ደግሞ "እንዲያው ለመሆኑ ይሄንን ነገር መለሰ ብለህ አይተኸዋል? ብዙሃኑ ሕዝብ የሚቀበለን አይሆንምና። ይሄን የመሥዋዕትነት ሕይወት እግዚአብሔር ይፈልገዋል?" ይለናል። ይሁን እንጂ ክርስቶስን የምንመስልበት ምስጢር ዋነኛው የመሥዋዕትነትን ሕይወት ለመኖር መፍቀድ ነው።

ጌታ በሉቃስ 14፥28-30 ላይ ሲናገር *"ከእናንተ ለንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራት ቢፈልግ መደምደም መቻል አለመቻሉን በመጀመሪያ ተቀምጦ ዋጋውን ያሚይተምን ማን ነው? መሠረቱን ጥሎ መደምደም ቢያቅተው ያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል፤ እንዲህም ይላሉ፤ ይህ ሰው ማነጽ ጀምሮ ነበር፤ መደምደም ግን አቃተው"* ይላል።

ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሳስብ ሁልጊዜ ወደ አእምሮዬ የሚመጣው አንድ ወንድማችን ነው። ይህ ወንድም እንድ ወቅት ቤት መሰራት ጀመረ። እናም እንድ ቀን ከሥራ አሰፈቅዶ ቀረና ቤቱን ወደሚሰራበት ቦታው ሄዶ ሲመለስ ብስጭት ብሎ መጣ። "ምን ሆነሃል?" አልኩት። "አይ ምን መሰለህ፤ እዚያ ቤቴን የማሰራበት ቦታ አጠገቤ ቤት መስራት የጀመረው ሰው ነጋዴ ነው። የእርሱ በየዕለቱ ወደ ላይ እየተገነባ ሲሄድ፤ የእኔ ግን ያው ታውቃለህ ባለበት ነው ያለው። እና ቆሜ ሳየው የመድሃኒዓለም ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲለቀቁ በአጠገባችን እያለፉ የጎረቤቴን የነጋዴውን ቤት ቶሎ ቶሎ መሰራት እያዩ አደነቁና ወደ እኔዋ ዘወር ብለው ደግሞ 'ይቺ ቤት መቼ ይሆን ተሰርታ የምታልቀው፤ ባለችበት ቆማ ቀረች እኮ' ሲሉ ሰማኋቸው። ይሄ አበሳጭቶኝ ነው" አለኝ።

ምክንያቱ ምንድነው ስንል? ይሄ ወንድም ቤቱ ከመጀመሩ በፊት ለማንባታው ሥራ የሚያስፈልገውን ግንዘብ መጠን እና በእጁ ላይ ያለውን መጠን ቁጭ ብሎ አስልቶ ባለመጀመሩ ከጅመረ በኋላ ግን ሊያጠናቅቀው ተሳነው። ጌታ የሚጠይቀን "ከእናንተ መካከል ቤት የሚሰራ፣ ቁጭ ብሎ ኪሳራውን የማይቆጥር ማን ነው?" ነው የሚለን።

ለዚህ ነው ጌታን ስንከተል አለቀድሞ ጌታ የሚፈልግብን ነገር ይመኙን ወይም አይመኙን እንደሆነ ቁጭ ብለን ሂሳባችንን መተመን የሚገባን። የምትከፍለውን ዋጋ፣ የምትሄድበትን መንገድ አርሱን አወቅ። ስንት እንደሚያስወጣህ፣ ስንት እንደሚቀርብህ መዝን ብሎ ይናገራል። ወይም ከንጉሥ መካከል ጦርነት ከመግጠሙና "ምታ ነጋሪት" ከተት ሠራዊት" ብሎ አዋጅ ከመለፈፉ በፊት ያለውን ነገር የሚይመዝን ማን ነው? እጥመዋሁ ወይ እችለዋለሁ ብሎ አቅሙን የማይፈትሽ ሰው ማን ነው? ልክ እንዲሁ አኔን የሚከተል ቢኖር አስቀድሞ የሚያስከፍለውን ዋጋ ይተምን ብሎ ነው የሚናገረው (ሉቃስ 14፥31-33)።

ክርስትናችን መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠትም ነው። ሕይወትን፣ ጸጋን፣ ደስታን፣ ፈውስን፣ በረከትን ተቀብለናል። ወደ አግዚአብሔር ቤት መጥቼ ብዙ ወንድሞችን እና እህቶችን አግኝቻለሁ። ውድ እና ብርቅ የሆኑ ወገኖችን አግኝቻለሁ። ግን ፈቅደን ስለ ጌታ ፍቅር፣ ለለ አግዚአብሔር መንግሥት ስንል የምንተወው፣ የምናጣው፣ የሚቀርብን፣ የምንነጠቀው፣ የሚወሰድብን የምንሰጠው ነገር ደግሞ አለ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ አርሱንና የትንሣኤውን ኃይል አውቅ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ ቆጠርኩት እንዳለው ሕይወት ማለት ነው። በሕይወታችን እንደዚህ የምንተዋቸው፣ የምንሰዋቸው፣ የምንክዳቸው ሦስት ነገሮች አሉ። እነርሱን ልንገራችሁ።

1. <u>ወዳጅነትን</u>

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14፥25 ላይ የተጻፈውን ቃል እንመልከት፤ እንዲህ ይላል። *"ብዙ ሕዝብ አብረውት ለየተጓዙ ሳለ፤ ኢየሱስ ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው፤ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እህቶቹን፣ የራሱንም ሕይወት እንኳን ሳይቀር ባይጠላ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም፤ የራሱንም መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም"*። ይሄ የጉበረትን ነገር ነው የሚያሳየን። ወዳጅነቶች አሉ።

ጌታ ይጠይቃል፤ እንድ ቀንም ሚዛን ላይ ያወጣናል። ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? ብሎም ይጠይቀናል። ስንቱ ስለ ጌታ ሲል የወንድሞቹን፣ የአህቶቹን፣ የባልንጀራውን ፍቅር ችላ ብሏል። ዕብራውያን መልዕክት ምዕራፍ 11፥17 ላይ አግዚአብሔር የሚወደውን፣ የሚሳሳለትን እንድ ልጁን ይስሐቅን እንዲሠዋለት በመጠየቅ አብርሃምን ፈተነው ይለናል። አብርሃም ልጁን ይዞ ወጣ፤ የፈተና መንገዱ ደግሞ አያልቅም፤ ረዥም ነው። ይገርማችኋል! ለምን የደቂቃ መንገድ አይሆንም የዘላለም ያህል ረዥም ነው። ቀጥ ያለው መንገድ ዳገታማ ይሆናል። እናም ሦስት ቀን ያህል ከተጓዙ በኋላ ልጁ "አባቴ የመሥዋዕቱ በግ የት አለ?" ሲለው፤ አባትየው ግን "አግዚአብሔር ያዘጋጃል" እያለው ልጁን ሊሰዋው በአግዚአብሔር ፊት አጋደመው። አብርሃም ይስሐቅ ቢሞትም አግዚአብሔር ከሞት ሊያስነሳው እንደሚችል ማመኑን የዕብራውያን ጸሐፊው በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 19 ላይ ይነግረናል።

አብርሃም፤ ከልጁ ከይስሐቅ ይልቅ አግዚአብሔር እንደሚበልጥበት ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ባለማመንታት እምነቱን በተግባር ገልጾ አሳይቷል። አግዚአብሔር ከጎብረቶቻችን ሁሉ ወዳጅነትን ይፈልጋል። በትዳር፣ በልጅ፣ በሥራ ባልደረባ እንዲሁም በማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነታችን ውስጥ ሁሉ አርሱን ማስቀደማችንን እና አለማስቀደማችንን ማወቅ ይፈልጋል። "ነፍሱን ለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ብሎ ራሱን ስለ እንተ የሰጠ ጌታ እናንተ በተራችሁ ምን እንደምትሰጡት ማወቅ ስለሚፈልግ መጥቶ ይፈትሻችኋል።

ሚስት ሲያገኝ ከርስቶስን ይተው እንደሆነ፣ ባል ሲታገኝ ከርስቶስን ትተው እንደሆነ፤ ከርስቶስን ከባልንጀሮቹ ይልቅ ወደ ኋላ ያደርገው እንደሆነ አግዚአብሔር ይህንን ማወቅ ይፈልጋል። ወገኖቼ ሆይ! ብዙ ሰዎች ለለ ኢየሱስ ከርስቶስ መተው ያቃታቸው ግንኙነቶች አሏቸው። ምናልባትም ባለን የትዳር፣ የኦሮ ግንኙነቶች ሊሆን ይችላል፤ በግንኙነቶቻችን ውስጥ ኢየሱስ ከርስቶስን እናከብረው። በእነዚያ ውስጥ እንኳን የማይመች ሁኔታ ቢኖር በዚያ ውስጥ ከርስቶስን አይተን፣ ከርስቶስን አስበን፣ ከርስቶስን ለማከበር ፈቅደን ታግሰን በመከራ የምንኖረው ኑሮ በአግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አለው። ይሄ የመሥዋዕትነት ሕይወት ነው።

2. <u>ራስን መካድ</u>

ሁሉም ነገር ዋጋ የምንከፍልበት የወዳጅነት ግንኙነት ነው ብያችኋለሁ።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14፥27 ላይ *"ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም"* ይላል።

መስቀል መሸከም ማለት ምን ማለት ነው? መስቀል መሸከም ቃል በቃል እንደ ተጻፈው እንገታችን ላይ መስቀል ማንጠልጠል አይደለም። መስቀል እንገታችን ላይ በማንጠልጠላችን እግዚአብሔርን ደስ ወደምናሰኝበት መንገድ መጓዝ የምንችል ቢሆን ኖሮ፤ ወገኖቼ ሁላችንም በውድድር ተሸቀዳድመን እያንዳንዳችን ቢያንስ አስር፣ አስር መስቀል በዓይነት በዓይነቱ በተለያየ መጠን አለርተን እናንጠለጥል ነበር። የቃሉ አውድ ሐሳብ የሚለው ግን እንደዚያ አይደለም።

መስቀል መሸከም ማለት ራስን መካድ ማለት ነው። ኢየሱስ ከርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን ለው የሚሸከመው መስቀል የጌጥ መስቀል ሳይሆን የስቅላት ሞት የሚፈጸምበትን ነው። ወንጀለኞች በሞት ፍርድ ሊቀጡ ሲሉ የሚሰቀሉበትን መስቀል የስቅላት ፍርዱ እስከሚፈጸምበት ቦታ ድረስ ያሸከሟቸው ነበር። ለዚህ ነው ኢየሱስ ከርስቶስን መስቀል ያሸከሙት።

ጌታ "ማንም ሊከተለኝ የሚወድ ቢኖር መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ ይከተለኝ" ብሎ ያለን እኔነታችን የሚሞትበትን መስቀል ነው። ሙሴ በፈርዖን ቤት ሲበላ እና ሲጠጣ እደገ፤ የግብጽንም ትምህርት ተማረ። ነገር ግን ሁሉን ሲያውቅና ነገሮችን መገንዘብ ሲችል ወይ ከከርስቶስ መከራ ተካፋይ ለመሆን ከሕዝቡ ጋር መወገን፤ አሊያም የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ ከብሩንና ዝናውን ጠብቆ የመኖር ምርጫ ወደ ሕይወቱ መጣ።

የእግዚአብሔር ቃል ሊናገር *"ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ። ለጥቂት ጊዜ ቢኖሐአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፤ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበል መረጠ። ከግብጽ ሐብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል ለጅግ የሚበልጥ ሐብት መሆኑን ተገነዘበ። ወደፊት የሚቀበለውን ብድራት ከራቅ ተመልከቷልና። የንጉሡን ቁጣ ላይፈራ ግብጽን ለቆ በእምነት ወጣ፤ የማይታየውንም እንዳየው ሊድርጎ በመቁጠር በሐሳቡ ጸና"* ብሎ ይናገራል (ዕብራውያን ዘ፥24-27)።

ወገኖቼ ሆይ! በየዕለቱ ከእንቅልፋችን ስንነቃ ይሄንን መስቀል ለመሸከም የመምረጥ ወይም በሌላ ተቃራኒ መንገድ ለመመላለስ የመምረጥ ምርጫው አለን። በየጊዜው በሕይወታችን፤ "ቢቃ ራሴን ለዚህ ነገር እንደ ሞተ ሰው መሰቀል አለብኝ" ብለን በውሳኔችን የምናውቀው፤ ነገር ግን ያቃተን ነገር ምን ይሆን? ዛሬ በእግዚአብሔር ቃል የማደፋፍራችሁ እና የማበረታታቸው እዚያ መስቀላችሁ ላይ እንድትቆዩ ነው።

ከመስቀላችሁ ላይ "ውረድ! ውረጂ!" የሚሏችሁ ነገራችሁን፤ ስሜታችሁን የሚጎትት ሲኖር አትንቀሳቀሱ። በመለቀሉ ላይ ራሳችንን እንደ ሞተ ሰው አድርገን ብንቆጥረው፤ ከሦስት ቀን በኋላ ትንሣኤ እና አዲስ ሕይወት፣ አዲስ ኑሮ አለና እንጨከን። ያንጊዜ የእግዚአብሔር ክብር በለኛ ይገለጣል። ብዙ ሰው ከመስቀሉ ወርዷል። መጨከን አቅቷቸው፣ መጽናት ተስኗቸው ከመሰቀሉ የወረዱ ለዎች በትንሣኤው ቀን ላይ የከበረውን የትንሣኤ ሕይወት ሳያዩ ቀርተዋል። እንዴት ያሳዝናል። ትንሣኤን ለማየት በመለቀሉ ላይ ራስን ከዶ መጽናት የግድ ይላል።

3. <u>የራስን ምኞት፣ ሐብት እና ንብረት ማጣት</u>

መሥዋዕትነትን የምንከፍልበት ሌላው ነገር ምኞታችን፣ ገንዘባችን እና ንብረታችን ሲሆን፤ የሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 14፥33 ላይ *"እንግዲህ ከለናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም"* በማለት በንብረት፣ በገንዘብ፤ ስለሚገኘው ምኞት ይናገራል።

ያገኙትን ዕቃ ሁሉ መስብሰብ ስለሚወዱ ለዎች አለባችሁ ታውቃላችሁ? እኔ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ እንድ ፕሮግራም ቤቴሌቪዥን ቀርቦ ተከታትያለሁ። የተለያዩ ዕቃዎችን ለብሰቦ የመያዝ ችግር ያለባቸው ለዎች አሉ። ቢቃ ዝም ብለው እንደ ውዳቂ ጣሳ፣ ያረጁ ጫማዎች፣ ባዶ ታኒካ፣ ስባራ ወንበር፣ የማይሰራ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ. ያሉ ምንም ዕቃ የማይቀራቸው፤ እየሰበሰቡ የሚያከማቹ ለዎች። ቅራቅንቦ፣ ትርኪምርኪውን ሁሉ እንድ ክፍል ውስጥ እሽጎ ማስቀመጥ።

ይህን አስመልከቶ የቀረበውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሰመለከት "ቪረ ለመሆኑ እነዚህ ለዎች እዚህ ሁሉ ዕቃ ውስጥ ተቀብረው እንዴት ሊኖሩ ቻሉ?" የሚል ጥያቄ አጭሮብኛል። ይሄ መቼስ እንድ ራሱን የቻለ በሽታ ነው። እንዲህ ባለ አባዜ የተለከፉትን እነዚህን ለዎች ካሉበት ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት የሥነ-ልቦና አማካሪዎች፣ የሕግ አዋቂዎች ወይም ጉዳዩ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ይመለከተናል የሚሉ የተለያዩ

ሰዎችን ጥረትን ይጠይቃል። እንዴ! ዓመታትን ያሰቆጠረ እና ያንን የበሰበሰ፣ አፍንጫ በጥሶ የሚጥልም መጥፎ ሽታ ያለውን ጉድ ሁሉ ነውኮ ታቅፈው የሚኖሩት። በዚያ ላይ ደግሞ ሌላ መሰል ዕቃ ከተገኘ ሰብስበው አምጥተው ይጭኑቢታል። ይሄ የሆነ ልከፍት ነው።

ሚግበሰበስ፣ ማጀል እንዴን በሌላው ላይ እየወሻሸቁ መቆለል። ታዲያ ይሄንን ፊልም ስመለከት ችግሩን የእነርሀ ሰዎች ብቻ ችግር አድርጌ አላየሁትም። ዓይናችንን ከፍተን ብንመለከት ይሄ ዓለም በሙሉ የተጠመደበት አባዜ ነው። ያው አኛም ራሳችን ያሉበን ልከፍት ነው። ያየነውን ሁሉ "ግዛው፣ ግዢው"፤ ተመሳሳይ ዕቃ አያለን ለሌለው እና ሰተቸገረ ሰው እንኳ እንዳንሰጠው "አስቀምጠው፤ ያኛው ቢበላሽብህ በዚህኛው ትጠቀማለህ፣ ሰብስበህ ቆልፍበት፣ እሽህ አስቀምጠው" የሚል ነገር በውስጣችን አለ አይደል! መሰብሰብ፣ ማጋበስ!

ሌላም አለ። ቤተሰቦቻችን ሆኑ ዘመዶቻችን እዚህ አሜሪካን አገር ለተለያየ ጉዳይ ሲመጡ አንዱ የሚስተዋለውና ፍጥጥ ግጥጥ ብሎ የሚወጣው ይኸው የመሰብሰብ ችግር ነው። በዚያው በአገር ቤት አሰተሳሰብ ቅኝት የኦሮ ደረጃ ሰሌት ይጠፈነጉና ባዶውን ጀሪካን፣ ላስቲኩን፣ ሰባራ ጃንጣላውን፣ ምንም አይቀራቸው ሁሉንም እየሰበሰቡ ያስቀምጣሉ። ሁሉም በየፊናው በመሰብሰብ ዘመቻ ይጠመዳል። ሥጋ፣ መቀነስ ለሌለው ሰው መስጠት፣ ማካፈል አይመቸውም። ሰይጣንም ያንን እናደርግ ዘንድ አይሻም።

መስጠት እምብዛም ይህች ዓለም የምታደንቀው ነገር አይደለም። ትዝ ይላችኋል የዚያች በቤተ መቅደስ (ምኩራብ) መባ ትሰጥ የነበረች ሴት ታሪክ? ጌታ እዚያ መባ ዕቃ ጋ ቆሞ ይመለከት ነበር። እኛ በቤተ ክርስቲያናችን በዓመት አንድ ጊዜ ሰው ሁሉ ፊት ለፊት እያየ መባ የምንሰጥበት ጊዜ አለን። ታዲያ በምንሰጥበት ጊዜ ምንድነው የምናደርገው፤ ፕሮግራሙን የሚመራው ሰው በመዝሙር እየመራን እያጨበጨብን ደስ አያለን እንዘምራለን። እርሱ እየተመለከተ ጌታን እያመሰገንን። ሁሉም ዓይኑን ከፍቶ ይመልከት እንጂ ፍጥጥ ብሎ የሚመለከት ሰው አይኖርም። ጌታ ግን በዚያ ቤተ መቅደስ ትኩር ብሎ ይመለከት ነበር። ሁሉም የፈለገውን እያመጣ ሲሰጥ ያቺ መበለት ሴትም ሳንቲሟን ጣለች።

እናም ጌታ ምን አሰ? እርሷ ከሁሉ አብልጣ ሰጠች። ሰምን? ትዳሯን ሁሉ ሰጥታለችና። የነበራትን ምቾት፣ ለእርሷ ብቻ አድርጋ ልትጠቀምበት ትችል የነበረውን ፈቅዳ በውዴታዋ ሰጥታለችና። ቤቷን፣ ትዳሯን ከኋላ ጥርቅም አድርጋ ዘግታ በመስጠት ኑሮዋን መሥዋዕት አድርጋለች። ጌታ የወደደላት ይህንን ነው። አግዚአብሔር የሚወደው ይህንን ነው።

ሌላኛዋ በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ የምናውቃትና ሰለ መሥዋዕትነት ከእርሷ አበክረን ልንማር የሚገባን ሴት በረሃቡ ዘመን ውሰጥ የእምነት ባለ ታሪክ በመሆን ጎልታ የወጣችውን ያቺ ሴት ናት።

ሰነቢዩ ጥቂት ዱቄት እና ዘይት አለኝ፣ እኔ እና ልጄ በልተነው ልንሞት ያስቀመጥነው አሰች። በቃ! ከዚያ ዘይት እና ዱቄት በኋላ ሞት እንጂ ሌላ ምንም ተከትሎ ሊመጣ የሚችል ክስተት አልነበረም። ግን ነቢዩ "ደህና አድርገሽ ሰርተሽ አቅርቢልኝ!" አላት። ወይ ግሩም! ይሄ ጥያቄ እኮ "ከረ ጭራሽ! ምን ሲደረግ!" የሚያስኝ ነበር። ሴቲቱ ግን እሺ ብላ የታዘዘችውን አደረገች። ጌታ እንዲህ ዓይነት ልብ ይስጠን! ከአግዚአብሔር ይሁን እንጂ፣ ድምጹን ሰምተን ይሁን እንጂ፣ ከመንፈሱ ምሪት እናግኝ እንጂ፣ መሥዋዕት ለመሆን ወደ ኋላ አንበል።

ነቢዩ "ግድ የላችሁም ጌታን ተስፋ አድርጉ፣ እኔ ከበላሁ በኋላ እርሱ የሚሠራው ሥራ አይታወቅም" የሚል ምንም ዓይነት ማጽናኛ ቃል አልተናገራትም። ይልቁንም "ደህና አድርገሽ ጋግረሽ አምጪው" ነው ያላት። እንዳዘዛትም ጋግራ አመጣችለትና ግጥም አድርጎ በላ። ከዚያ በኋላ የቀራትን ኑሮ መቀጠል ነው። ነገር ግን ለሦስት ዓመት ያህል ስትኖር ጌታ ይህን የመሰለ መሥዋዕትነት ለከፈለችው ሴት ዋጋ ሰጥቶ ተዓምራቱን አትረፈረፈላት። ሰው ተጎድቶ፣ ሊጠቀምበት የሚችለውን ነገር ለቆ አግዚአብሔር ለሚከብርበት ሥራ፣ ለተቸገሩ ሰዎች፣ መለጠት ሲጀምር አግዚአብሔር ለዚያ ነገር ዋጋ ሰለሚሰጥ የጓዳቸውን ጉድለት በተዓምራት ይሞላላቸዋል። አትረፈረፋት።

ሐዋርያው ጳውሎሰ የፊልጵስዩስ አማኞች በገንዘብ ይደግፉት ሰለነበር በጣም ነበር የሚወዳቸው። ከዚህም የተነሳ በፊልጵስዩስ መልዕከቱ ምዕራፍ 4፣18 ላይ *"ከሚያስፈልገኝ በላይ ተቀብያለሁ፣ የላካችሁትንም ስጦታ ከአፍሮዲጡ እጅ ተቀብዬ ተምልቶአለሁ፣ ይህም መዓዛው የጣፈጠ በአግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ደስ*

የሚያሰኝ መሥዋዕት ነው" ብሎ ይናገራል።

ያለንን ነገር ስናካፍል፣ በጉድለታችን ስናገለግል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል። ውኖቼ መሥዋዕትነት ባለው በዚህ ሕይወት ጌታን እንድንመስለው እግዚአብሔር ይፈልግብናል። ይሁንና ይህንን በምንለማመድበት ጊዜ ግን ልባችሁ በእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ሊሆን ይገባል። ጌታ የሚንም ባለ ዕዳ ስላይደለ በጓላ ላይ መቆ እጥፍ የማያገኝ፣ መጽናናትንም የማይቀበል የለም። "እንባን ከዓይናቸው ያብሳል" ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሄ በአሁኑ ዘመን በመሥዋዕትነት በመሄድ የምታፈሱትን እንባ፣ የምትታገሉትን ትዕግስት፣ ስለ እርሱ የምታልፉብትን መንገድ በሙሉ እንድ በእንድ መዝግቦ ከዓይኖቻችሁ እንባን ያብሳል። በሐዘን ፈንታ የደስታ ጊዜን ይሰጣችኋል። ስለ ተቀበላችሁት መከራ የአረፍትን ጊዜ ትቀበላላችሁ። ባልታወቃችሁበት፣ በተናቃችሁበት ዘመን ፈንታ በእግዚአብሔር የታወቃችሁ ሆናችሁ በቤቱ ከብራችሁ የምትኖሩበትን ቀን እግዚአብሔር ያመጣዋል። የእግዚአብሔር ስም ብሩክ ይሁን!

ምዕራፍ 7

ወዳጅነትን አጥብቁ!